መስከረም 20/ 2000 ዓ.ም.
የወ/መ/ቁ.43246

ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
2ኛ ወንጀል ችሎት
<u>አዲስ አበባ</u>

ከሣሽ:- የፌደራል ዐቃቤ ሕግ
ተከሣሾች:- እነ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል (131 ተከሣሾች)

94ኛ ተከሣሽ:- ዳንኤል በቀለ
የአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ የፖሊሲ ዲፓርትመንት ሥራ አስኪያጅ

95ኛ ተከሣሽ:- ነፃነት ደምሴ
የማሕበራዊ ፍትሕ በኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ

## በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 148 መሠረት ከ94ኛ እና ከ95ኛ ተከሣሾች ቀረበ የመከላከያ ክርክር መደምደሚያ

### መግቢያ

ተከሣሾች በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 148 መሠረት የክርክር መደምደሚያ አስተያየታችንን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡
ለዚህ የክርክር መደምደሚያ አስተያየት አስፈላጊ በሆነው መጠን ድረስ በቅድሚያ የክሱን ይዘትና የዐቃቤ ሕግን ማስረጃዎች እንዲሁም የክሱን ሒደት በአጭሩ በመግለጽ፣ በመቀጠልም የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች በተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃዎች ሙሉ በሙሉ የተስተባበለ መሆኑን እና የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በማስረዳት ተከሣሾች ከቀረበብን ክስ በነፃ ልንሰናበት የሚገባ መሆኑን እናስረዳለን፡፡

# ማውጫ


ገጽ

ርዕስ

1. የዐቃቤ ሕግ ክስ 1

2. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች 2

2.1 የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች 2

2.2 የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች 5

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይን 13

4. የመከላከያ ክርክር ጠቅላላ መግለጫ 16

4.1 የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ቁጥር 2 በተመለከተ 17

4.2 የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ቁጥር 3 እና 62 እንዲሁም የዐቃቤ ሕግ ምስክር ንግስት መኳንንት በተመለከተ 17

4.3 የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ቁጥር 52 እና ምስክሮቹን በተመለከተ 22

4.4 የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ቁጥር 65 እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች (አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዩም) በተመለከተ 24

4.5 የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች (መሠረት ወርቁ እና ንግስት መኳንንት) በተመለከተ 31

4.6 የሲቪል ማኅበረሰቡ እንቅስቃሴና ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት 37

4.7 ስለ ተከሣሾች ባሕሪና አስተዋጽኦ 41

4.8 ስለ ተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃዎች ብቃት 50

5. ማጠቃለያ 53

## 1. የዐቃቤ ሕግ ክስ

1.1 ሁለታችንም ተከሣሾች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አባሎች ስንሆን ፤ ዐቃቤ ሕግ በእነ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል (የተቃዋሚው የቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባሎች ፣ ጋዜጠኞችና ሌሎች ተከሳሾች በድምሩ 131 ሰዎች) ላይ "ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሐይል ለመለወጥ የመሞከር ወንጀል" በሚል በአቀረበው ክስ በ94ኛ እና 95ኛ ተከሳሽነት ክስ ቀርቦብናል::

1.2 የክሱም ይዘት "...ተከሳሾች በወንጀል ሕግ ቁጥር 27(1) ፣ 32 (1) (ሀ) እና (ለ)፣ 34 ፣ 38 እና 238 (2)/258 የተመለከተውን በመተላለፍ በሕገመንግስትና በሥርዓቱ ላይ ወንጀል በመፈጸም፤ ሕገመንግሥቱንና በሕገመንግሥቱ መሠረት የተቋቋመውን ሥርዓት ለማፍረስ በአድማ በግብረአበርነት የሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል..." የሚል ሲሆን ፤ በተለይ የሁለታችን ተከሣሾች ድርጊትና ተሳትፎ ያመለክታል ተብሎ በክሱ ማመልከቻ አራተኛ ክፍል የተገለጸው "...ተከሳሾቹ የሚወክሉትን ማህበር ከተመሰረተበት ዓላማና ተግባር ውጪ በማንቀሳቀስ [ለወንጀሉ] ማስፈጸሚያና መጠቀሚያ በማድረግ ፣ በማህበራቱ ስም ውሳኔ በማሳለፍ ፣ መግለጫ በማውጣት ፣ በመቀስቀስ ፣ የማህበሩ አባላቶች የአመጽ ተግባሩን እንዲደግፉ በማነሳሳታቸውና አመራር በመስጠታቸው፣ ወጣቶች በአመጽ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በመገፋፋታቸውና በመደገፋቸው" የሚል ነው::

1.3 ዐቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት ክሱን ሲመሰርት ለተለያዩ ተከሣሾች ይመለከታቸዋል ያለውን የሰነድ ማስረጃዎች በፍርድ ቤቱ ፊት የሰጠ ሲሆን ፤ እኛን ሁለታችንን ተከሣሾች በሚመለከት ግን አንዳችም የሰነድ ማስረጃ አለማቅረቡና በሁለታችን ተከሣሾች ላይ የአቀረበውን ክስ በሰው ምስክሮች አስረዳለሁ ማለቱ ተመዘገበ::

1.4 በዚሁ መሰረት የክሱ ሒደት ከቀጠለ በኋላ ፤ ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም. ዐቃቤ ሕግ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ የሰነድ ማስረጃ ለማቅረብ ጠየቀ:: ተከሣሾችም ዐቃቤ ሕግ ፈጽሞ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ውጪ ያቀረበውን ጥያቄ ተቃወምን ፤ ፍርድ ቤቱም ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ. ም. በሰጠው ትዕዛዝ ፤ ዐቃቤ ሕግ ክሱን በመሰረተ ጊዜ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ የሰነድ ማስረጃ አለማቅረቡን ፣

ይልቁንም በሁለታችን ተከሣሾች ላይ የአቀረበውን ክስ በሰው ምስክሮች አስረዳለሁ ማለቱን ፣ የክሱ ሒደት በዚሁ መሠረት ከቀጠለ በኋላ በመካከሉ የሰነድ ማስረጃ ለማቅረብ መፈለጉ ከሥነ ሥርዓቱ ሕግ ውጪ መሆኑን በመግለጽ የዐቃቤ ሕግን ጥያቄ ውድቅ አደረገ::

1.5 አሁንም በዚሁ መሠረት የክሱ ሒደት ቀጥሎ ዐቃቤ ሕግ በሌሎች ተከሳሾች ላይ የአቀረበውን የሰነድ ማስረጃዎችን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ፣ ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ጥያቄ አቀረበ::

ሁለታችንም ተከሣሾች ከዚህ በላይ እንደገለጽነው ማናቸውም ዓይነት የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበብንና ፣ ዐቃቤ ሕግ በእኛ በተከሣሾች ላይ የክሱ ሒደት ከተጀመረ በኋላ የሰነድ ማስረጃ ለማቅረብ ጠይቆ ውድቅ የተደረገ ስለሆነ ፣ የተጨማሪ ሰነድ ማስረጃው ጥያቄ ሁለታችንን ተከሣሾች የማይመለከት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ አመለከትን::

1.6 ሆኖም ፍርድ ቤቱ ሐምሌ 7 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ዐቃቤ ሕግ በእኛ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ ጭምርም ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ሊያቀርብ ይችላል በማለት ትዕዛዝ ሰጠ:: በዚሁ መሠረትም ዐቃቤ ሕግ በሁለታችን ተከሣሾችና በሌሎችም ተከሳሾች ላይ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች ያለውን ሰነዶች አቀረበ::

## 2. <u>የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች</u>

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ዐቃቤ ሕግ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ የሰነድ ማስረጃዎችና የሰው ምስክሮች አቅርቧል:: የሁለቱም አይነት ማስረጃዎች ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው::

### 2.1 <u>የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች</u>

2.1.1 ዐቃቤ ሕግ በሌሎችም ተከሳሾች ላይ ጭምር በርካታ የሰነድ ማስረጃዎች የአቀረበ ሲሆን ፣ ከእነዚህ ውስጥ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ እንደ ክሱ አቀራረብ ያስረዳልኛል በማለት መግለጫ ያቀረበባቸው 4 (አራት) ሰነዶችን ብቻ ሲሆን ፣ እነዚህም የተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 3 ፣52፣ 62 እና 66

ብቻ ናቸው፡፡ (ሐምሌ 17/1998 የተጻፈው የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ፡፡)

2.1.2 ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ "ተጨማሪ ማስረጃዎች" በማለት ያቀረባቸው ሰነዶች ምን ያህል ተገቢ እንዳልሆኑና የዐቃቤ ሕግ ጠቅላላ አሰራሩም የቱን ያህል ሕጋዊነት እና ቅን ልቡና የጎደለው መሆኑን ለማሳየት እንችል ዘንድ በሁሉም የሰነድ ማስረጃዎች ላይ መግለጫ ለመስጠት እንወድ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ፍርድ ቤት ለሰጠው ብይን መሠረት ባላደረጋቸው ማስረጃዎችና ፍሬ ነገሮች የፍርድ ቤቱን የስራ ጊዜ ላለማባከን ፤ ፍርድ ቤቱ ለብይኑ መሠረት በአደረጋቸው አምስት የሰነድ ማስረጃዎች ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 2 ፡- "የግንቦቱ ምርጫ ሒደትና አገራችን የምትገኝበት አጣብቂኝ" በሚል ርዕስ ተቃዋሚው የቅንጅት ፓርቲ በይፋ ለሕዘብ ውይይት የአቀረበው ሰነድ፣

(ለ) ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 3 እና 62፡- ነሐሴ 2/1997 የተጻፈ የሲቪል ማህበረሰቡ የግማሽ ቀን ስብሰባ ሪፖርት እና የግንቦት 1997 ምርጫን ተከትሎ የተፈጠረው የፖለቲካ ውጥረትን በሚመለከት የሲቪል ማህበረሰቡ የአቀረበው የሰላም ጥሪ (ነሐሴ 3/1997)

(ሐ) ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 ፡- ኤልያስ ክፍሌ የተባሉ ሰው ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ኃይሌ ለተባሉ ሰዎች የጻፉት ደብዳቤ ነው የተባለ ሰነድ እና

(መ) ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 65 ፡- አዳነ በቀለ የተባለ ሰው ነፃነት ደምሴ ሰጥቶኛል የሚላቸው በራሪ ወረቀቶች ናቸው፡፡

(ስለእነዚህ ሰነዶች ይዘት በየደረጃው በዝርዝር እናስረዳለን፡፡)

2.1.3 እነዚህ የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች በሙሉ ለፍርድ ቤቱ ሊቀርቡ የማይችሉ ወይም የማይገባቸው (inadmissible) ስለመሆናቸው ተከሣሾች በርካታ የሕግ መቃወሚያ ክርክሮችን አቅርበን ነበር፡፡ የመቃወሚያ ክርክሮቹ ዋነኛ ነጥቦች በአጭሩ፡-

(ሀ) ማስረጃ ተብለው የቀረቡት ሰነዶች በሕገወጥ መንገድ የተገኙ ስለመሆናቸው (ማስረጃ ቁጥር 2፣ 3 ፣52 እና 62 ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጪ በጠመንጃ ኃይል በተደረገ ሕገወጥ ብርበራ የተወሰዱ ሰነዶች

ስለሆኑ ፤ የሕገወጥ ተግባር ፍሬ እንደ ሕጋዊ ማስረጃ ሊቀርብ የማይችል መሆኑን)፣

(ለ) ማስረጃ ተብለው የቀረቡት ሰነዶች ትክክለኛ ወይም እውነተኛ (authentic or genuine) ያልሆኑ፣ ዋናው ሰነድ ሳይቀርብ ተገቢ ባልሆነ አሰራር ከዋናው ሰነድ እንደተመሳከሩ በማስመሰል የቀረቡ ግልጽ የሆኑ የፈጠራ ሰነዶች (manufactured evidence) መሆናቸውን (ማስረጃ ቁጥር 52 እና 65 ይመለከታል)፣

(ሐ) ማስረጃ ተብለው የቀረቡት ሰነዶች በፍርድ ቤት ማስረጃነት ሊቀርብ የማይችል የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (hearsay evidence) ስለመሆኑ (ማስረጃ ቁጥር 52 እና 65 ይመለከታል) ፣

(መ) ማስረጃ ተብለው የቀረቡ ሰነዶች በፍርድ ቤቱ ለተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ አግባብነት (relevance) የሌላቸው ሰነዶች ስለመሆኑ (ተጨማሪ ማስረጃዎቹን በሙሉ ይመለከታል) ፣ እንዲሁም

(ሠ) ማስረጃ ተብለው የቀረቡ ነገር ግን ምን ፍሬ ነገር እንደሚያስረዱ መግለጫ ያልቀረበባቸው ሰነዶች ሊቀርቡ የማይችሉ (inadmissible) ስለመሆኑ የቀረበ መቃወሚያ ክርክር ነበር፡፡ (ማስረጃ ቁጥር 2 እና 65 ይመለከታል)

(ተከሣሾች ስለ ዐቃቤ ሕግ ሰነድ ማስረጃዎች ሊቀርብ የማይችል ወይም የማይገባ (inadmissible) ስለመሆኑ ያቀረብነውን ዝርዝር የሕግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦች ሐምሌ 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ተጽፎ በአቀረብነው አቤቱታ ገልጸናል፡፡)

2.1.4 ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ የተገለጸውን መቃወሚያ በሚመለከት ጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ብይን የተከሣሾችን የመቃወሚያ ክርክሮች ባለመቀበል እና የማስረጃዎቹ ብቃት ወደፊት በክርክሩ ሒደት የሚመዘን መሆኑን በመግለጽ የዐቃቤ ሕግን የሰነድ ማስረጃዎች ከመዝገቡ እንዲያያዙ አድርጓል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለጸው ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ስለአቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችና ማስረጃዎቹ ስለቀረቡበት ሒደት ሲሆን ከዚህ በመቀጠል የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ስለቀረቡበት ሒደት እና የሰጡት የምስክርነት ቃል በአጭሩ እንገልጻለን፡፡

## 2.2. የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች

2.2.1 ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ክሱን በመሰረተበት ወቅት ለምስክሮቼ ደህንነት እሰጋለሁ በሚል ሰበብ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ማንነት ለተከሣሾች ሳይገለጽ በሚስጥር ይጠበቅልኝ በማለት ለፍ/ቤቱ አመልክቶ ነበር፡፡ ተከሣሾች የቀረበብንን ክስና ማስረጃዎች በሙሉ የማወቅ እና የማየት መብታችንን ፣ የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች ማንነት አስቀድመን በማወቅ ለመስቀለኛ ጥያቄ ተዘጋጅተን የመምጣት መብታችንን ፣ የዳኝነት ሒደቱ በግልጽ ችሎት የሚካሄድ መሆኑን፣ ማንኛውም ተከሣሽ የቀረበበትን ክስና ማስረጃዎች በሙሉ የማየት ሕገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑን ፣ የምስክሮች ማንነት በሚስጥር የማስጠበቅ መብት የተከሣሽ እንጂ የከሣሽ የዐቃቤ ሕግ አለመሆኑንና በአጠቃላይ የተከሣሾችን የመከላከል መብት መሠረት በማድረግ እና ጥያቄውም በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለጽ የዐቃቤ ሕግን ጥያቄ ተቃውመን ነበር፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ የተከሣሾችን ተቃውሞ ባለመቀበሉ፣ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ማንነት አስቀድሞ ሳይገለጽልን ምስክሮቹን የመስማት የክሱ ሒደት ቀጥሏል፡፡

2.2.2 የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ፍርድ ቤት ከቀረቡና ቃላቸውን ከሰጡም በኋላ ፣ ዐቃቤ ሕግ የምስክሮቹ ማንነት በሚዲያ እንዳይገለጽ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት አመልክቶ ነበር፡፡ ተከሣሾች አሁንም የዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ፊጽሞ ከፍትሐዊና ግልጽ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መርህ እና መብት (The right to fair and public trial) ውጪ መሆኑን ፣ ዐቃቤ ሕግ ስለገለጸው ስጋት አንዳች እንኳን ማስረጃ ወይም አሳማኝ ሁኔታ አለመግለጹ፣ ስጋት አለ ቢባል እንኳን እንደ የሁኔታው ከባለጉዳዩ አሳማኝ ጥያቄ ሲቀርብ የሚታይ እንጂ በደፈናው በግልጽ የዳኝነት ሒደት ላይ ክልከላ ሊደረግ እንደማይገባ በመግለጽና የተከሣሾችን በግልጽ ችሎት የመዳኘትና የመከላከል መብት መሠረት በማድረግ ፣ የዐቃቤ ሕግን ጥያቄ ተቃውመን ነበር፡፡

ሆኖም ፍርድ ቤቱ የተከሣሾችን ተቃውሞ ባለመቀበል ፣ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ፊት ቀርበው ከመሰከሩም በኋላ ማንነታቸው በሚዲያ እንዳይገለጽ በማለት አዟል፡፡ (ከፍተኛው ፍ/ቤት ጥቅምት 15 እና ጥቅምት 17/1999 የሰጠው ትዕዛዝ፡፡)

2.2.3 ከዚህ በላይ በተገለጸው ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ በመጀመሪያ አራት ምስክሮች ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደግሞ ተጨማሪ ምስክሮች ለማቅረብ ጠይቆና በፍ/ቤቱ ተፈቅዶለት ሶስት ምስክሮች ፤ በአጠቃላይ ሰባት ምስክሮች አሰምቷል፡፡ የምስክሮቹም ቃል በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

2.2.4 ወ/ሮ መሠረት ወርቁ የተባሉ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆኑ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 24/1999 ከዚህ በታች የተመለከተውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡-

"... ዳንኤልና ነፃነትን የማውቃቸው ምርጫ 97 አካባቢ ነው፡ ለሲቪል ሶሳይቲ ምርጫ ታዛቢዎች ስልጠና ተዘጋጅቶ ነበር ፣ ስልጠናውን ያዘጋጁት እነርሱ ናቸው ፣ ሲሰጥ የነበረው ትምህርት ኢሕአዴግ ሌባ ነው ምርጫውን ያጭበረብራል ተጠንቀቃችሁ ጠብቁ ፣ ኢሕአዴግ ማታ መብራት ስለሚያጠፋ ባትሪ እናዘጋጃለን የሚል ነገርም ሲነገር ነበር ፣ እንደ ሲቪል ሶሳይቲ ሳይሆን ልክ እንደተቃዋሚ ሆነው ነበር ስልጠናውን ይሰጡ የነበሩት ፣ እኔ በጣም ግር ሲለኝ ነበር ፣ ይሄ የግል አስተያየቴ ነው ፣ ከዚያም በኋላ በCRDA አዳራሽ ኦሬንቴሽን ተሰጥቶን ነበር ፣ ዳንኤልና ነፃነት ነበሩ ፣ እዚያም ላይ ሁኔታው ጥሩ አልነበረም ፣ የምርጫ ታዛቢዎች በየቦታው ስንደለደል እነሱ የሚፈልጉበት ቦታ መደቡን ፣ እኔ ከቤቴ ሩቅ የሆነ ቦታ መደቡኝ ፣ ባትሪ የተሰጠን ምናልባት መብራት ቢጠፋ ስራችን እንዳይሰናከል ተብሎ ነው ፣ የስነ ምግባር ደንብ ተሰጥቶን ነበር ፣ ምን እንደሚል አላስታውስም ፣ የምርጫ መታዘቡን ስራ ስሰራም የስነ ምግባር ደንቡን አላስታውስም ፣ ዳንኤልና ነፃነት ይምታቱብኛል ፣ ዳንኤል የትኛው ነው ነፃነት የትኛው ነው በግልጽ አለያቸውም ፣ ከሁለት አንዳቸው ግን ነበሩ ፣ ሁለቱ ልዩነት የላቸውም ፣ ሁለቱም አንድ አይነት ነው ሐሳባቸው ፣ እኔ ዋነኛ ቅሬታዬ ከቤቴ ሩቅ ቦታ መመደቤ ነው ፣ ከዚህ ውጪ ሌላ ቅሬታ የለኝም፣ በእርግጥ ታዛቢዎችን በየቦታው መደልደል የእነሱ ኃላፊነት ነው ፣ እኔ ግን ቅርብ ቦታ ይመድቡኛል ብዬ አስቤ ሩቅ ቦታ መደቡኝ፣ ቤቴ አቃቂ ቃሊቲ ነው ፣ እነሱ ልደታ መደቡኝ ፣ በሌሊት ልደታ ድረስ እንድሄድ..." በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡፡

2.2.5 ወ/ሮ ንግስት መኪንንት የተባሉ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 24/1999 ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል :-

"... ሐምሌ 29/1997 ቀይ መስቀል አዳራሽ የተደረገው የሲቪል ሶሳይቲ ምክክር ስብሰባ ላይ ነበርኩ ፣ አርፍጄ ነበር የደረስኩት ፣ ተቃዋሚዎች ፓርላማ ይግቡ ወይስ አይግቡ ውይይት ነበር ፣ የእኛ [ሲቪል ማህበሩ] ድርሻ ምን ይሁን የሚል ነበር ፣ ከቤቱ ግን መንግስት አፋኝ ነው : ጨቋኝ ነው ፣ ምርጫው ተጭበርብሯል ፣ 229 ምርጫ ጣቢያዎች እንደገና ምርጫ መካሄድ አለበት ፣ ሚዲያ ጆሮአችንን አያደንቁር ፣ ያለፈው ተወካዮች ምክር ቤት አሳሪ የሆነ ሕግ አውጥቶ ስለሄደ ብንገባም ችግር ነው ፣ ባንገባም ችግር ነው ስላሉ ምን ይደረግ የሚል ነው ፣ እነ ዳንኤል በ299 ምርጫ ጣቢያ ተጭበርብሯል መንግስት አፋኝ ነው ብለዋል ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት መቋቋም አለበት የሚሉ ነገሮችን ይናገሩ ነበር ፣ ... በሌላ ጊዜ ደግሞ የምርጫ ታዛቢዎች ኢትዮጵያ ሆቴል ስብሰባ ላይ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ኢሕአዴግን ደግፋችሁ ሰልፍ ልትወጡ ነው የሚል ነገር ተነስቶ መብታችን ነው አይደለም በሚል በስፋት ተከራክረናል ተወያይተናል ፣ ዳንኤል በከፍተኛ ተቃውሞ ተከራክሮኛል ፣ እናንተ ኢሕአዴጎች ናችሁ ብሎኛል ፣ በቀይ መስቀል አዳራሽ ስብሰባ ዳንኤልና ነፃነት አንድ አይነት አነጋገር ነበራቸው ፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም ፣ ነፃ ምርጫ ቦርድ ይቋቋም የሚል ነገርም ነበር ፣ ዛቻ ነገር ወይም እንዲህ እናደርጋለን የሚል ነገር አልነበረም..." በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ::

2.2.6. አቶ አዳነ በቀለ የተባለ ስራው ደላላ መሆኑን የገለጸ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥቷል:-

"…. ነፃነት ደምሴን አውቀዋለሁ፣ አንድ ሰፈር ነን፣ ኢሕአዴግ ምርጫውን ስላጭበረበረ ለአመጽና ለሁከት የአካባቢያችንን ወጣቶች እንዳደራጅ እየነገረኝ ሰርቻለሁ፣ ሃያና ሰላሳ ብር ይሰጠኝ ነበር፣ በዚሁ መሠረት ወጣቶች አስተባብሬ አጥር አፈራርሰናል፣ ጐማ አቃጥለናል፣ …. የሚበተን ወረቀት ሰጥቶኛል፣ …. ዳንኤልም ጥቂት ቀን ተገናኝተን ተመሳሳይ ነገር ነግሮኛል፣ ዳንኤልን ያስተዋወቀኝ ነፃነት ነው፣ ሌላ ቀን ደግሞ በድንገት መንገድ ላይ ተገናኘን፣

መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ ወጣቱን ለአመጽ እንቅስቃሴ እንዳዘጋጅ እንዳስተባብርና እንዳደራጅ ነገረኝ፣ በዚሁ መሠረት ሰራሁኝ፣ .... ያስተባበርኩትና ያደራጀሁትን ሰዎች ስማቸውን አላውቅም፣ የአንድ ሰውም ስም አላውቅም፣.... ከአካባቢያችን ሰዎችም ሌሎችም ሰዎች አስተባብሬያለሁ፣ መጠጥ ቤትም አደባባይ ላይም የማገኛቸውን ሰዎች አስተባብሬያለሁ፣ አንድ ቀን ብቻ ያገኘሁትንም ሰዎች አስተባብሬያለሁ፣ .... ሻይ ቡና የሚጠጡ ሰዎችን በተቀመጡበት ሄጄ አነጋግሬ አሳምናቸውና ለአመጽ ዝግጁ አደርጋቸዋለሁኝ ፣ በአንድ ቡና ቤት ውስጥ አንድም፣ ሁለትም፣ አስራ አምስት ሰውም ከዚያም በላይ ማስተባበር እችላለሁ፣ ይሄን ሁሉ ብቻዬን ነው የምሰራው፣ የአካባቢውን ሰው አስተባብሬ አውቶቡስ እና ታክሲ አስቆምን፣ የኢንቨስተሮችን አጥር አፍርሰን አወደምን፣ ከእነዚህ ካስተባበርኳቸው ሰዎች ውስጥ አንድም ሰው ስሙን የማስታውሰው የለም፣ ስለዚህ ሁኔታ ለቤተሰቦቼም ወይም ለሌላ ለሰፈር ጓደኞቼም ለማንም አልተናገርኩም፣ እነሱም ጠይቀውኝ አያውቁም፣ ነፃነት የሰጠኝ የሚበተን ወረቀቶች ለማላውቃቸው ሰዎች ሰጠሁኝ፣ ታክሲ ላይ ለማገኛቸው ሰዎች እሰጣለሁ፣ ሁኔታቸውን እያየሁ ወሬ ለማስነሳት እሞክርና አነጋግራለሁ፣ ድምፅ መጭበርበሩን በአመጽ ኢሕአዴግን ስለመጣል ጉዳይ ታክሲ ውስጥ ለማገኛቸው ሰዎች አነጋግራቸዋለሁ፣ ወረቀት እሰጣቸዋለሁ ቀደም ሲል የቀበሌ አስተዳደር ነበርኩ፣ .... በኋላ ተጸጽቼ እጄን ለፖሊስ ሰጠሁ፣ ስሙን አላውቀውም፣ ስትፈለግ ትጠራለህ አለኝ፣ .... ከዚያ ፖሊስ ቤቴ መጥቶ ጠራኝ፣ ከቤቴ ማንም ሰው አላየም፣ አልሰማም እኔም አልተናገርኩም፣ ለእናቴም አልነገርኩም፣ ለፖሊስ የሰራሁትን ተናገርኩ ፣ ቀኑን አላስታውስም፣ ፖሊስ በድጋሚ ሲጠራኝ እቤቴ ድረስ መጥቶ በር ሲያንኳኳ በአጋጣሚ እኔ ከፈትኩለት፣ ፖሊሱን ስሙን አላውቅም፣ ፖሊሱ መምጣቱን ከቤትም ይሁን ከሰፈር ያየው ሰው የለም፣ ፖሊሱ በነገረኝ መሰረት አንድ ቢሮ ሄጄ ፖሊስ አነጋገረኝ፣ ቢሮ ቁጥሩንም ስሙንም አላስታውስም፣ ቀኑንም አላስታውስም ....” በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥቷል።

2.2.7 አቶ ወንድወሰን ስዩም ዳዲ የተባለ ፣ ስራ አጥ መሆኑን የገለጸ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም. ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥቷል፡-

#...... ዳንኤል በቀለን አውቀዋለሁ፣ በአጋጣሚ ነው የተዋወቅሁት፣ አንድ ሻይ ቤት ውስጥ ከሰው ጋር ሻይ ስጠጣ ነበር፣ የምናወራውን ሰምቶ ወጣት

ስለሆንኩኝ በርታ አለኝ፣ ስልኩን ሰጥቶኝ አንድ ሁለት ጊዜ አገኘሁት፣ ወጣቶችን እንዴት ማስተባበርና ማደራጀት እንደሚቻል፣ ስለ ወረቀት መበተን፣ አድማ ማድረግ፣ ህዝቡን ማስተባበር፣ መንግስትን መገልበጥ ነገረኝ፣...... ሁለት መቶ ብር ሰጠኝ፣ ወጣቶችን በዚሁ መሰረት አደራጀሁኝ፣ በአጋጣሚ በመንገድ የማገኘውን ሰውም ሁሉ ቀስቅሻለሁ አስተባብሬያለሁ፣ ...... እነዚህን ያስተባበርኩትንና ያደራጀሁትን ሰዎች የአንድም ሰው ስሙን አላውቅም፣ ዳንኤልን ለመጀመሪያ ጊዜ በአጋጣሚ ያገኘሁት ከሻይ ቤት ሲወጣ ነው፣ ብቻውን ነበር፣ እኔም ከሻይ ቤት ስወጣ ነበር፣ ከዚያ በፊት አላውቀውም፣ እንዴት ነው ወጣቶች ምን እየሰራችሁ ነው? ምን እንቅስቃሴ እያደረጋችሁ ነው ብሎ ጠየቀኝ፣ ብቻዬን ነበርኩ፣ በግምት ሁለት ደቂቃ ተነጋገርን፣ ከዚህ በላይ የተባለውን መመሪያ በሙሉ የሰጠኝ በዚሁ በሁለት ደቂቃ ውስጥ ነው፣ ከዚህ በኃላ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ያገኘሁት ከአንድ ከአስራ አምስት ቀን በኃላ ነው፣ እቢሮው ድረስ ሄጄ አገኘሁት፣ በአጋጣሚ ነበር፣ ቢሮ ሄጄ አቶ ዳንኤል ቢሮአቸው እዚህ ነው ወይ ብዬ ጠይቄ አዎን አሉኝ፣ ከዚያ ዳንኤል መጣ ተገናኘን፣ ከቢሮ ሲወጣ ነው ያገኘሁት፣ ስልክ ደውዬለት ነው የመጣው፣ ከሱቅ ሚስድ ኮል አደረኩ እንጂ በስልክ አላነጋገርኩትም፣ ሚስድ ኮል አድርጌ ወደ ቢሮው አካባቢ መጣሁ፣ ግቢው ውስጥ አልገባሁም፣ ቻይና ሬስቶራንት አካባቢ መንገድ ላይ ቆሜ ጠበኩት፣ ብቻዬን ነበርኩ፣ እዚህ ጋር ነኝ ብዬ ምልክቴን ነገርኩት፣ መጥቶ አገኘኝ፣ ከዚህ ቀን ውጪ ደውዬም ተገናኝተንም አናውቅም፣ ሁለት መቶ ብር ለማደራጃ ብሎ ሰጠኝ፣ ብሩን አደራጀሁበት፣ በአጋጣሚ የማገኘውን ሰው ሁሉ እግረ መንገዴን ሳገኘው አደራጀዋለሁ፣ የማደራጃቸውን ሰዎች ስማቸውን አላውቀውም፣ ከአካባቢዬም ከሌላ ሰፈርም አደራጃለሁ፣ በየመንገዱ ሰውን እያስቆምኩ አደራጀዋለሁ፣ መንገደኛውን አስቆምና ለውጥ አትፈልጉም ወይ? ለውጥ እናምጣ እላቸዋለሁ፣ መንገደኛውም ለውጥ ስለሚፈልግ እሺ ነው የሚለው፣ ከዛም ወረቀት እሰጣቸዋለሁ፣ ወረቀቱ ምን እንደሚል አላውቀውም፣ ከዛ ቀጠሮ አድርጌ አገኛቸዋለሁ፣ ብዙ ጊዜ አግኝቻቸዋለሁ፣ ያገኘኋቸውንም ሰዎች ስማቸውን አላስታውሰውም፣ በመንገድ ላይ እየተገናኘን ነው የምንነጋገረው፣ ከዚያ በኋላ እኔ ተሰውሬ ነበር፣ እራቅ ብዬ ሄድኩ፣ ሳሎ ሄድኩኝ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ነው፣ አድራሻውን አላውቀውም፣ ተሰውሬ በነበረ ጊዜ አንድ ሌላ ሰው ቤት

ተቀመጥኩ፣ ሰውየውን አላውቃቸውም፣ የማላውቀው ሰው ቤት ተደበቅሁኝ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደተሰወርኩም አላውቀውም፣ ከዚያ ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ እጄን ሰጠሁ፣ ስሙን አላስታውስም፣ ፖሊሱ ያነጋገረኝ ለብቻዬ ነበር፣ አንድ ቢሮ ውስጥ ገባሁና ቃሌን ሰጠሁኝ፣ ቃሌን የተቀበለኝ ፖሊስ ስሙን አላስታውሰውም፣ ፍ/ቤት ሲፈልግህ ስትጠራ ትመጣለህ ብሎኝ ሄድኩ፣ የኢ.ዴ.አ.ፓ. አባል ነበርኩ፣ ዳንኤልን አንድ ቀን ከታምራት ጋር መንገድ ላይ ቆሞ አይቼዋለሁ፣ ከዳንኤል ጋር እንደተዋወቅሁኝና ከእርሱ ጋር ስላደረግነው ነገር ለድርጅቴም ወይም ለሌላ ሰው ለማንም አልነገርኩም ፣......; በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥቷል ፡፡

2.2.8 ከዚህ በላይ ከተገለጹት አራት ምስክሮች በተጨማሪ ዐቃቤ ህግ ተጨማሪ ምስክሮች ለማቅረብ ጠይቆ በተፈቀደለት መሰረት ሶስት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል።

ዐቃቤ ሕግ እነዚህን ተጨማሪ ሶስት ምስክሮች ያቀረበው ከዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች ውስጥ በተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 ተመዝግቦ ያቀረበው ሰነድ ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ሃይሌ ከተባሉ ሰዎች ቤት በፍተሻ የተገኘ ስለመሆኑ ያስረዳሉ በማለት ነው።

ይህ ሰነድ አንድ ኤልያስ ክፍሌ የተባሉ ሰው ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ሃይሌ ለተባሉ ሰዎች የጻፉት ነው የተባለ ደብዳቤ ሲሆን፤ በወረቀቱ ሁለተኛው ገጽ የመጨረሻው ፓራግራፍ ላይ #...... ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ የቅንጅቱ [ተቃዋሚው ፓርቲ ቅንጅት] አገናኝ መኮንኖች (Contact Persons) እንደሆኑ በአቶ ኃይሉ ሻውል የተገለጸልን በመሆኑ ከእነርሱ ጋር ተገናኝታችሁ አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ......; የሚል ሀረግ አለው። እንደ ዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ መሠረት ይህ ወረቀት እንዲያስረዳ የተፈለገው ጭብጥ ልክ በወረቀቱ ላይ በተገለጸው ዓይነት ሁለታችን ተከሣሾች የተቃዋሚው ፓርቲ “አገናኝ መኮንኖች (Contact Persons)” ናቸው ለማለት ነው።

2.2.9 ይህ ኤልያስ ክፍሌ በተባሉ ሰው ተጻፈ የተባለው እኛ ተከሣሾች ፈጽሞ የማናውቀው ወረቀት:-

- ደብዳቤውን ጽፈዋል የተባሉት ሰው ፊርማ የለውም፣ ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት ማረጋገጫ የለውም፣
- ደብዳቤው ተጽፎላቸዋል የተባሉት ሰዎች ለእነሱ የተጻፈ ደብዳቤ መሆኑን አላረጋገጡም፣
- ከላይ በተራ ቁጥር 2.1.5 ስር እንደገለጽነው የዚህ ደብዳቤ ዋናው ቅጂ ለፍርድ ቤቱ ሳይቀርብ ልክ ዋናው ቀርቦ እንደታየ በማስመሰል ተገቢ ባልሆነ አሰራር #ከዋናው ጋር ተመሳክሯል; ተብሎ የቀረበ ፎቶ ኮፒ የሆነ ወረቀት ነው፣
- ተከሣሾች የደብዳቤውን ጸሀፊም ሆነ ደብዳቤው ተጻፈላቸው የተባሉትን ሰዎች በሙሉ አናውቃቸውም።

ይህን ወረቀት ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ሃይሌ ከተባሉ ሰዎች ቤት የተገኘ ስለመሆኑ ያስረዳሉ የተባሉት ሶስት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ከዚህ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል:-

2.2.10 አቶ ተፈሪ ሀይሉ የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምስክር ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል:-

"... በ20/05/98 ከፒያሳ ወደ ቤቴ በእግሬ እየሄድኩ ነበር፣ ዮሃንስ ቤተክርስቲያን አካባቢ ስደርስ አንድ ፖሊስና ሲቪል [የለበሰ ሰው] ከፖሊስ መኪና ወርደው አንድ የሆነ ቤት ልንፈትሽ ነው በታዛቢነት ለማየት ተባበረን ብለውኝ ፈቃደኛ ሆንኩና ገባን፣ አንድ የታሰረ ሰው ከፖሊስ ጋር መጣ፣ ብርሃነ ሃይሌ ነው፣ ቤቱ የእሱ እንዳልሆነና የሚያርፍበት ቤት ስለሆነ ባለቤቱን ጥሩልኝ አለ፣ ሲቪል [የለበሰው]ሰውዬ ስልክ ደውሎ አነጋገረ፣ ምን እንደተነጋገረ አላውቅም፣ በኋላ ሲያወራ እንደሰማሁት ሰውየው እኔ እሩቅ ቦታ ነኝ ሌላ ሰው ከፍቶ ሊያሳያችሁ ይችላል ስለተባለ አንዲት ሴት ልጅ ተጠርታ [መጣችና ቤቱን ከፍታልን] ገባን፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነበረ፣ እኔ ትዕዛዙ ምን እንደሚል አላየሁትም፣ ቤቱ ተከፍቶ ከገባን በኋላ የተለያዩ በርካታ ሰነዶች ተወሰዱ፣ ከኤልያስ ክፍሌ ለብርሃነ ሃይሌ

የተጻፈ የተባለውን ደብዳቤ አስታውሳለሁ፣ ከቤቱ ውስጥ በተወሰዱት ሰነዶች ላይ እንዲፈረምባቸው ተደርጓል ፣ ብርሃነ ሃይሌ በወረቀቶቹ ላይ ዝም ብሎ ነው የሚፈርመው፣ ማን እንደሰጠው፣ ለምን እንደያዘው አልተጠየቀም፣ ምንም የቀረበለት ጥያቄ የለም፣ ብርሃነ ሃይሌ በወቅቱ የተናገረው ነገር ሀ?~ የእርሱ እንዳልሆነና በእንግድነት ስመጣ የማርፍበት ቤት ነው የሚል ብቻ ነው ፣ ከኤልያስ ክፍሌ የተጻፈ የተባለው ደብዳቤ ላይ ከመፈረሙ በፊት አንድ ነገር ሲጽፍ አይቸዋለሁ ፣ የጻፈውን ግን አላነበብኩትም ፣…" በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡፡

2.2.11 አቶ አዳሙ ለገሰ የተባሉ የቀበሌ ሰራተኛ መሆናቸውን የገለጹ የዐቃቤ ህግ ምስክር ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡-

#…የፍሬዘር ቤት ሲፈተሽ ከቀበሌው አስተዳደር ታዝዤ ተገኝቻለሁ፣ ፖሊስ ቤቱን ለመበርበር ፈቃድ መያዙን አላየሁም…; ካሉ በኋላ ዐቃቤ ህግ በተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 መዝግቦ ያቀረበው ከኤልያስ ክፍሌ ለፍሬዘር ነጋሽ ተጻፈ የተባለውን ደብዳቤ ምስክሩ ይመልከቱትና በታዛቢነት ፊርማቸውን መፈረማቸውን ያረጋግጡልን ብሎ በመጠየቁ ፍ/ቤቱ ሰነዱን ለምስክሩ እንዲሰጥ አደረገ። ምስክሩም ሰነዱን ከተመለከቱ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ምስክርነት ቃል ሰጡ።

#…በዚህ ሰነድ ላይ የእኔ ፊርማ ያለው በአንድ ገጽ ላይ ብቻ ነው፣ በመጀመሪያው ገጽ ላይ ብቻ ነው ፊርማዬ ያለው፣ በሁለተኛው ገጽ ላይ ፊርማዬ የለም [ሁለተኛው ገጽ ከላይ በተራ ቁጥር 2.2.8 እና 2.2.9 ስር እንደገለጽነው ስለ ሁለታችን ተከሣሾች የፈጠራ ዓረፍተ ነገር የተጻፈበት ገጽ ነው] ፣ የመጀመሪያውን ገጽ አስታውሳለሁ፣ ሁለተኛው ገጽ ከዚያው ቤት ይገኝ አይገኝ አላስታውስም፣ ፊርማዬም የለበትም፣ እኔ የፈረምኩት በመጀመሪያው ገጽ ብቻ ነው፣ ደብዳቤው ዘዋሪ ገጽ እንዳለውም አላስታውስም፣ በዚህ ሰነድ ላይ ፍሬዘር አልፈረመችም [ፍሬዘር ነጋሽ ይህ ሰነድ የእኔ ነው በማለት አላረጋገጠችውም]…; በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡፡

2.2.12 ወ/ት መርሻ ተሾመ የተባሉ የቀበሌ ሰራተኛ መሆናቸውን የገለጹ የዐቃቤ ህግ ምስክር ከዚህ በታች የተገለጸውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡-

"...የፍሬዘር ቤት የተጠራጠርነው ነገር ስላለ የምንፈልገው ዕቃ ካለ ስናወጣ ቆመሽ እንድታይ ነው ተብዬ ተወሰድኩ፣ ሰዎቹ በመኪና ይዘውኝ ሄዱ፣ እሷንም [ፍሬዘር ነጋሽ] በመኪና ይዘዋት መጡ፣ በቦታው ስንደርስ ፖሊስ ቤቱን ከቦታል ፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መኖሩ ትዝ አይለኝም፣ ቤቱ ተፈትሾ ብዙ ዶክመንቶች ከወጣ በኋላ ይሄንን ነው የምንፈልገው ፈርማችሁበት ይዘነው እንሄዳለን አሉ፣ ፈረምንበት፣ ዝርዝሩን አላስታውሰውም..." ካሉ በኋላ ዐቃቤ ህግ በተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 ያስመዘገበውን ሰነድ ምስክሯ እንዲመለከቱ ጠይቆ ሰነዱን ከተመለከቱ በኋላ የሚከተለውን ገልጸዋል።

#...በዚህ ወረቀት በሁለቱም ገጽ ላይ ፊርማዬ አለ፣ በወቅቱ ብዙ ሰነዶች ነበሩ፣ ይዘቱን አላስታውስም፣ ፍሬዘር በወቅቱ አንድ ወረቀት ላይ አልፈርምም ብላ በጣም ስትከራከር ነበር፣ የቱ ወረቀት እንደሆነ አላስታውስም፣ ይሄ ወረቀት የእኔ አይደለም እያለች ነበር ስትከራከር የነበረው፣ ወረቀቶቹን ከቤቱ ውስጥ ከያለበት እየሰበሰቡ ያነሱ የነበሩት መርማሪዎቹ ናቸው፣ እኛ እዛ ስንደርስ ፖሊሶች ግቢው ውስጥ ነበሩ፣ ቤቱ ተቆልፎ እንደነበር ትዝ አይለኝም...; በማለት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል::

ከዚህ በላይ የተገለጸው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሠረት ተከሣሾች በቀረበባቸው ክስ መሠረት የተመሰከረባቸው ስለሆነ ክሱን ሊከላከሉ ይገባል ወይስ እንደ ክስ አቀራረቡ የተመሰከረ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሆኖ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በሚለው ጭብጥ ላይ ከዚህ በታች የተመለከተውን ብይን በድምፅ ብልጫ ሰጥቷል::

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይን

3.1 የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሁለታችን ተከሣሾች ላይ በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ብይን የሚከተለውን አስፍሯል፡-

- ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት የተሰባሰቡት አመራሮች ምርጫው ተጭበርብሯል፣ የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም ፣ጥምር መንግስት ይቋቋም በማለት ሕገ-መንግስታዊ ስርአቱን በሀይል ለማፍረስ የአመጽ ተግባር ሲያካሂዱ 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች ይሄንኑ የወንጀል አድራጐት በሙሉ ሃሳባቸው በመስማማት ፣
- የሲቪል ማህበረሰባዊ ድርጅት ከመሰረታዊ አላማው ውጪ በሆነ አኳሃን ፖለቲካዊ ስራ እንዲሰራ በማሰብ፣
- ቅድመ ምርጫ ኢሕአዴግ በምርጫው ሂደት ያጭበረብራል ፤ ከምርጫው በኃላ ደግሞ ምርጫው ተጭበርብሯል በሚለው አቋማቸው በመጽናት ፣
- መንግስት በምን ዓይነት ሁኔታ መመስረት እንዳለበት በሕግ የተወሰነ መሆኑ እየታወቀ ሕግ በማይፈቅደው አሰራር ጥምር መንግሰት ይቋቋም የሚለውን ፍላጐታቸውን በማራመድ ፣
- ከፖለቲካ ፖርቲዎች ጥቅም የሃገር ጥቅም ይቅደም በሚለው [የሲቪል ማህበሩ] መግለጫ ካሰፈሩአቸው ጉዳዮች አንዱ ፓርቲዎች አሸናፊነታቸው የተረጋገጠላቸውን ወንበሮችን በመቀበል ወደ ፓርላማ እንዲገቡ የሚል ሃሳብ የተገለጸበት ቢሆንም ፤ ሌሎቹ የዚህ መግለጫ ይዘቶች የሚያመለክቱት ተከሳሾቹ በሌሎች ሰነዶቻቸው እንዳሰፈሩትና በቃልም በየአጋጣሚው መናገራቸው እንደተመሰከረባቸው ፤ የምርጫ ውጤት መጭበርበሩን ፤ የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑን ጐልቶ የታየበት በመሆኑ ፣
- ይህ ደግሞ የሲቪል ማህበረሰቡ በመንግስትና በተቃዋሚ ቡድኖች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር አዎንታዊ መግለጫ አስተላልፏል ከሚያሰኝ ይልቅ በምርጫው ሂደት ከፍተኛ ማጭበርበር አለ የሚለውን [ የተቃዋሚዎችን] አቋም የሚያጐላ በመሆኑ ፣
- ዐቃቤ ሕግ በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ካቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ውስጥ በኤልያስ ክፍሌ ለእነ ፍሬዘር ነጋሽ ተጻፈ የተባለው እንደ አካባቢ ማስረጃ ሊቆጠር ከሚችለው ሰነድ በስተቀር ሌሎቹ ሰነዶች በጥቅሉ ሲመረመሩ ተከሳሾቹ በምስክሮቹ የተነገረባቸውን የወንጀል ድርጊት መፈጸማቸውን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ፣
- የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በግልጽ እንደሚታየው ከዋናው ጭብጥ አንፃር በማይቃረን ሁኔታ የተመሰከረ በመሆኑ ፤

- ስለሆነም ተከሳሾቹ የቀረበባቸው ክስ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸው ስለሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) ፣27 (1)፣ እና 238 (1) (2) ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል::

(መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የተነበበው የብይኑ ክፍል ከገጽ 9 እስከ 12 ::)

3.2 ከዚህ በላይ ከተገለጸው የአብላጫው ድምጽ ውሳኔ በሐሳብ የተለዩት የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ ከዚህ በታች በአጭሩ የተገለጸውን የሐሳብ ልዩነታቸውን አስፍረዋል::

- ክሱ ሕገ-መንግስታዊውን ስርአት በሀይል ለማፍረስ ሙከራ ማድረግ የሚል ሲሆን ከዚህ አንፃር አሳማኝ ማስረጃ አለመቅረቡን ፣
- በተለይ አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዩም የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ቃል አጠራጣሪና ሊታመን የማይችል እንደሆነ ፣
- ኤልያስ ክፍሌ የተባሉ ሰው ለእነ ፍሬዘር ነጋሽ የጻፉት ነው የተባለው ደብዳቤ በተከሳሾች ላይ ብቃት ያለው ማስረጃ እንዳልሆነ ፣
- ተከሳሾች በሲቪል ማህበሩ ውይይት አንስተውታል የተባለው ሐሳብ በውይይት ጊዜ የቀረበ ሐሳብን በነፃ ከመግለጽ አንፃር የሚታይ እንጂ የጥምር መንግስትም ሆነ ሌላ በሃይል ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል በማለት የተንቀሳቀሱ መሆኑን የሚያሳይ እንዳልሆነ ፣
- ማንም ሰው የሽግግር መንግስት ይመስረት የሚልም ቢሆን ሌላ የመሰለውን ሃሳብ ቢያራምድ የዛቻ፣ የሃይል፣ የአድማ ወይም የአመጽ ተግባር ጋር ካላቆራኘው በስተቀር ስለተወያየ ብቻ ወንጀል ፈጽሟል ለማለት እንደማይቻል ፣ ወንጀል የሚሆነው ይህንን ሲያራምድ የቆየውን ሃሳብ ከሕገመንግስት ውጪ በሃይል ሊያሳካው ሲሞክር እንደሆነ ፣
- ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም ሲቪል ማህበረሰቡ ያወጣው መግለጫም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ተከሳሾችም ሆነ ሌሎች በራሳቸው ግምት እና እምነት አማራጭ ብለው ያቀረቡት ሐሳብ እንጂ የወንጀል ይዘት ያለው አለመሆኑን፣
- ስለሆነም ሁለቱ ተከሣሾች የቀረበባቸው ክስ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ከአብላጫው ድምጽ ውሳኔ በሐሳብ መለየታቸውን ገልጸዋል:: (መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በሰብሳቢው ዳኛ የተነበበው የብይኑ ክፍል ከገጽ 13 እስከ 18)

4. <u>የመከላከያ ክርክር ጠቅላላ መግለጫ</u>

ዐቃቤ ሕግ የሁለታችንን ተከሣሾች የወንጀሉ ተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታ በማለት ያቀረበው "...የሚወክሉትን ማህበር ከተመሰረተበት አላማና ተግባር ውጪ በማንቀሳቀስ [ለወንጀሉ] ማስፈጸሚያና መጠቀሚያ በማድረግ በማህበራቱ ስም ውሳኔ በማሳለፍ፣ መግለጫ በማውጣት፣ በመቀስቀስ የማህበሩ አባላቶች የአመጽ ተግባሩን እንዲደግፉ በማነሳሳታቸውና አመራር በመስጠታቸው፣ ወጣቶች በአመጽ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በመገፋፋታቸውና በመደገፋቸው" የሚል ነው:: ወንጀሉ የተባለውም መንግስትን በሃይል ለመገልበጥ መሞከር ነው::

በዚህ መሰረት ዐቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ በሆነ መስፈርት (beyond a reasonable doubt) እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት ተከሳሾች በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወይም በመላ አሳባቸውና አድራጎታቸው በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆንና ድርጊቱን የራሳቸው በማድረግ በኃይል፣ በዛቻ፣ በአድማ ወይም ሕገወጥ በሆነ በማናቸውም መንገድ አስበው ሕገመንግስቱንና ሥርአቱን ለማፍረስ፣ ለመለወጥ ወይም ለማገድ በመሞከር ወንጀል መፈጸማቸውን ነው::

ሆኖም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ፈጽሞ እንደ ክስ አቀራረቡ እንደማያስረዳ፣ ይልቁንም ክሱና ማስረጃው እንደሚቃረን እና በተጨማሪም ክሱና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በሙሉ በተከሣሾች የመከላከያ ክርክር ሙሉ በሙሉ የተስተባበለ ስለመሆኑ እንደሚከተለው እናስረዳለን::

በተለይም ተከሣሾች የቀረበብንን ክስ እንድንከላከል በማለት ፍርድ ቤቱ ከሰጠው ብይን አንጻር እንድናስተባብል የሚጠበቅብን በመሆኑ፤ በዚሁ መሠረት ለብይኑ መሠረት የሆኑ የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎችና የሰው ምስክሮችን በሚመለከት በተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ የተስተባበሉ መሆኑንና፤ ስለሆነም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ብቃትና ተዓማኒነት የሌላቸው እንደሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እናስረዳለን::

## 4.1 የዐቃቤ ሕግ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 2 በተመለከተ

በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 2 ስር ተመዝግቦ የቀረበው ሰነድ ተቃዋሚው የቅንጅት ፓርቲ በይፋ ለሕዝብ ውይይት የአቀረበው ሰነድ ነው:: ይህ ሰነድ በፓርቲው የኢንተርኔት ድረ ገጽ ( web site ) የሚገኝ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲው በአዲስ አበባ ከተማ በልዩ ልዩ ወረዳዎች በአደረገው ስብሰባ ለተሳታፊዎች ያቀረበው ወረቀት ነው:: የቅንጅት ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት የተከሣሾች 153ኛ መከላከያ ምስክር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በሰጡት የምስክርነት ቃል ሰነዱን የጻፉት እርሣቸው እንደሆኑ፣ ተቃዋሚው ቅንጅት ፓርቲ ከሕዝብ ጋር ለሚያደርገው ውይይት እንደመነሻ ሐሳብ እንዲረዳ ብለው በቅንጅት ፓርቲ ስም የአዘጋጁትና ለሕዝብ የቀረበ ሰነድ መሆኑን እንዲሁም በፓርቲው የኢንተርኔት ድረ ገጽ (web site) ጭምር እንደሚገኝ አረጋግጠዋል:: ይህ ሰነድ በ94ኛ ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ በመገኘቱ ብቻ እንደ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተቆጥሮ ቀርቧል:: የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ሰነድ ለምን አያችሁ? ለምን አነበባችሁ? ይባልበት ወደነበረው የጨለማና ድንቁርና ዘመን አሽቆልቁለን ካልሆነ በስተቀር ይህ ሰነድ በተከሣሽ ቢሮ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎችም እጅ የሚገኝ ነው:: ለነገሩ ዐቃቤ ሕግም ከሰነድ ማስረጃዎቹ ጋር በደፈናው አያይዞ አቀረበው እንጂ ስለ ሰነድ ማስረጃዎቹ በአቀረበው መግለጫ ይህ ሰነድ ምን ፍሬ ነገር እንደሚያስረዳለት ምንም ያቀረበው መግለጫ አልነበረም::

## 4.2 የዐቃቤ ሕግ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 3 እና 62 እንዲሁም የዐቃቤ ሕግ ምስክር (ንግስት መኳንንት) በተመለከተ

4.2.1 በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 3 እና 62 ስር ተመዝግቦ የቀረበው ማስረጃ የሲቪል ማህበረሰቡ የስብሰባ ሪፖርት እና የሰላም ጥሪ ሰነድ ነው:: እነዚህ ሁለት ሰነዶች የሚገልጹት:-

(ሀ) የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ የተፈጠረው የፖለቲካ ውጥረትና አጣብቂኝ ያሳሰባቸው የሲቪል ማህበሮች ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. እና ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. ተሰብስበው በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታና በሲቪል ማህበሮች ሚና እንደተወያዩ፣

(ለ) በእነዚህ ስብሰባዎች የተነሱት ሦስት አብይ ጭብጦች:-

- በተቃዋሚ ፓርቲዎች ፓርላማ የመግባትና አለመግባት ጥያቄ የተፈጠረው የፖለቲካ አጣብቂኝ እና የሲቪል ማህበረሰቡ አስተያየት ምን መሆን አለበት የሚል ጥያቄ፣
- የኢትዮጵያን የዲሞክራሲ ሒደት ለዘለቄታው ከማጠናከርና ሰላምን በሐገሪቱ ከማስፈን አንፃር የሲቪል ማህበረሰቡ ሚና እና
- የሲቪል ማህበረሰቡ በዚህ ቀጣይ ሒደት ውስጥ ምን ሚና ሊኖረው ይገባል የሚል እንደነበር፣

(ሐ) የሲቪል ማህበረሰቡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. የሲቪል ማህበረሰቡ የሰላም ጥሪ ይፋ መደረጉ፤ በዚህ የሰላም ጥሪ የተላለፉት ዋነኛ ነጥቦችም:-

- ሁሉም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ውሳኔ አሸናፊነታቸው የተረጋገጡላቸውን የፓርላማ ወንበሮች በመረከብ ወደ ፓርላማ እንዲገቡና በሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ መሠረት ስልጣን የሚረከበው መንግስት እንዲመሰረት፣
- ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቅሬታ ያነሱባቸውን የምርጫ ክልሎች ውጤት በሚመለከት ቅሬታዎች በፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲወሰኑ፣
- ምርጫውን ተከትሎ የተፈጠረው ውዝግብ ያስከተለው ሁከት እና የሰው ሕይወት መጥፋት ሁኔታ የሚያጣራ ገለልተኛ አካል እንዲቋቋም፣
- ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ (ፍትሐዊ የሚዲያ አጠቃቀም፣ የፓርላማ አሰራር የሥነ ሥርዓት ደንቦች ማሻሻል፣. . .) የሚሉ ናቸው::

4.2.2 የሲቪል ማህበረሰቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሐምሌ 29 ቀን 1997 እና ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. ከአደረጋቸው የሁለት ቀን ስብሰባዎች ውስጥ በአንደኛው ቀን ብቻ ማለትም ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በቀይ መስቀል ስብሰባ አዳራሽ በተደረገው ስብሰባ ላይ ስብሰባው ከተጀመረ በ|ላ አርፍደው መድረሳቸውን የገለጹት ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተከሣሾች "...ምርጫ ተጭበርብሯል፣ መንግስት አፋኝ ነው፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም፣ ነፃ ምርጫ ቦርድ ይቋቋም" የሚል ነገር ተናግረዋል በማለት የምስክርነት ቃል መስጠታቸው ይታወሳል:: (ተራ ቁ. 2.2.5)

4.2.3 ይሁንና ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በቀይ መስቀል አዳራሽ እና ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል አዳራሽ በተካሄዱት ስብሰባዎች ላይ ከስብሰባዎቹ አዘጋጅነት አንስቶ እስከ ተሳታፊነት ተገኝተው የነበሩ አራት የተከሣሽ መከላከያ ምስክሮች (27ኛ፣ 123ኛ፣ 134ኛ እና 155ኛ ምስክሮች) በተመሳሳይ መልክ እና ቃል በሰጡት የምስክርነት ቃል ከዚህ በታች የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች ተረጋግጠዋል፡-

ሀ. በሁለቱም የሲቪል ማህበሩ ስብሰባዎች ሁለታችንም ተከሣሾች በወቅቱ ለነበረው የፖለቲካ አጣብቂኝ ሰላማዊና ሕጋዊ መፍትሔ ለማስገኘት መስራታችንና መድከማችን፣

ለ. ተከሣሾች በስብሰባው ላይ የሰጠነው አስተያየትና የአራመድነው ሐሳብ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ወደ ፓርላማ እንዲገቡ፣ ክርክር ያስነሱ የምርጫ ጣቢያዎች ጉዳይ በፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን የሚል እንደነበር፣

ሐ. ሁለታችንም ተከሣሾች ከዚህ ውጪ ፀረ- ሰላም የሆነ፣ ሕገወጥ የሆነ፣ ወገንተኛ የሆነ ንግግር ፈጽሞ እንዳላደረግን፣ ይልቁንም በገለልተኝነትና በሙያዊ አቀራረብ ጭምር ለሕጋዊና ሰላማዊ መፍትሔ በትጋት መድከማችንን፤ ስለሆነም የዐቃቤ ሕግ ምስክሯ የተናገሩት ፈጽሞ ትክክል አለመሆኑን በተጨባጭ ሁኔታ አስረድተናል፡፡

4.2.4 ከተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮች በተጨማሪም የተከሣሾች የሰነድ ማስረጃዎች ይህንኑ ሁኔታ በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ሀ. በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 17 ስር የቀረቡት ሰነዶች ተከሣሾች ተሳታፊ የነበሩበት የሲቪል ማህበረሰቡ የሰላም ጥሪ ሒደት ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ መካሄዱንና፤ የሰላም ጥሪውም በግልጽ ለሕዝብ ይፋ መሆኑን ያረጋግጣሉ፣

ለ. በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 1 እና 2 ስር የቀረቡት ተከሣሾች ከተለያዩ ጋዜጦች ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ ዘገባዎች በሙሉ በተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮች በአንድ ዓይነት ቃል በተመሰከረው ዓይነት ሁለታችንም ተከሣሾች ለሰላማዊና ሕጋዊ መፍትሔ ያደረግነውን ጥረት በተለይም፡-

- በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ አጣብቂኝ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርድ የተረጋገጠላቸውን ወንበሮች በመረከብ ወደ ፓርላማ መግባትና ቅሬታ ያስነሱ የምርጫ ውጤቶችን በሚመለከት በፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን የማድረግ አስፈላጊነት መግለጻችን፣
- ተፎካካሪ ፓርቲዎች የምርጫውን የፉክክር ዘመቻ ያጠናቀቁ ስለሆነ ከእንግዲህ በሕግ፣ በሥነ ሥርዓት፣ በቅንነትና በሐቀኝነት መስራት እንዳለባቸው፤ በምርጫው ፉክክር የተነሳ የተካረረውን የፖለቲካ ውጥረት በማርገብ ከእንግዲህ በጋራ አብሮ ማሰብ፣ አብሮ ማቀድ፣ አብሮ መስራት አስፈላጊ እንደሆነና በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ብቻ መራመድ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ አበክረን ማሳሰባችን፣
- በተለይም በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 2.2 ላይ እንደተመለከተው የጋዜጣው ዜና ዘገባ እና ቃለ ምልልስ የተካሄደው ይህንኑ ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በቀይ መስቀል የስብሰባ አዳራሽ የተካሄደውን ስብሰባ በሚመለከት ሲሆን በተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮች የተገለጸውን ፍሬ ነገር በተጨባጭ የሚያረጋግጥ መሆኑ፣
- በአጠቃላይ ሁለታችንም ተከሣሾች በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ውጥረት በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ሊፈታ የሚገባበትን መንገድ በጽናት በማሳሰብና በአጠቃላይ የነገሩ ሁኔታ ሚዛናዊ አስተያየት ከመስጠት ውጪ አንዳችም ጊዜ ሕገወጥ፣ ፀረ ሰላም፣ ወይም ሌላ ማናቸውንም ይህን የመሰለ ዓላማና ተግባር ላይ ተሰማርተዋል ሊያሰኝ የሚችል ተግባር አለመፈጸማችንን በተጨባጭ ያስረዳሉ:: (የሰነድ ማስረጃዎቹ ስለሚያስረዱት ጭብጥ ዝርዝር መግለጫ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈው የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ ላይ ቀርቧል::)

**4.2.5** ከዚህ በተጨማሪም የቅንጅት ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት 153ኛ የመከላከያ ምስክር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና 70ኛ መከላከያ ምስክር አቶ ደርበው ተመስገን በአንድ ዓይነት ቃል በሰጡት ምስክርነትም ሁለታችንም ተከሣሾች ቅንጅት ፓርቲ በአይቤክስ ሆቴል አዘጋጅቶት በነበረው የምክክር ስብሰባ ላይ ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሕጋዊና ሰላማዊ የመፍትሔ ሐሳብ አቅርበን ያስረዳን መሆኑን በማረጋገጥ መስክረዋል::

4.2.6 ከዚህ ሁሉ በተጨማሪም ሁለታችንም ተከሣሾች ተሳታፊ በነበርንበት ሌላ የዜጐች የሰላማዊ መፍትሔ ጥረት ውስጥ ተከሣሾች ስለነበረን ሕጋዊና ሰላማዊ አስተዋጽኦ በምስክሮችና በሰነድ ማስረጃዎችም አረጋግጠናል፡-

ሀ. የተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮች ውስጥ 10ኛው ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ፣ 12ኛ ዶ/ር ቆንጂት ፈቃደ፣ 141ኛ አቶ ታምራት ከበደ፣ 146ኛ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፣ እና 155ኛ ወ/ት ብዙወርቅ ከተተ በአንድ አይነት ቃል በሰጡት ምስክርነት ሁለታችንም ተከሣሾች ምርጫውን ተከትሎ የተከሰተው የፖለቲካ ውጥረትና አጣብቂኝ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈታ ስለአደረግነው ጥረትና አስተዋጽኦ እንዲሁም ከዚህ ሰላማዊና ሕጋዊ መፍትሔ አጀንዳ ውጪ በሌላ ፀረ-ሰላምና ሕገወጥ ዓላማና ተግባር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳላራመድን በተጨባጭ ሁኔታ በማረጋገጥ መስክረዋል፣

ለ. በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 18 ስር የቀረቡት ሰነዶችም ይህንኑ ተከሣሾች ስለ ሰላማዊና ሕጋዊ መፍትሔ ያደረጉትን ጥረት በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ (የሰነድ ማስረጃዎቹ ስለሚያስረዱት ጭብጥ ዝርዝር መግለጫ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈው የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ ላይ ቀርቧል፡፡)

4.2.7 ከእነዚህ ሁሉ በተጨማሪም በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 20.2፣ 20.3 እና 20.4 እንደተመለከተው በ94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ላይ መሳሪያ የታጠቁ ሰዎች ስለአደረሱት ድብደባና ጉዳት በተመለከተ "ኢፍቲን" ከተባለው ጋዜጣ ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት አንድ የገዢው የኢሕአዴግ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን በሰጡት ቃል "...ዳንኤል በቀለ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፓርላማ ይግቡ የሚል አቋም እንዳለው ይታወቃል፣ ይህን ሐሳቡንም በይፋ አራምዷል፣ ስለሆነም ያስደበደቡት ፓርላማ መግባት የሚቃወሙት የቅንጅት ፓርቲ ሊሆን ይችላል..." በማለት መናገራቸው ተከሣሹ ስለ ሕጋዊና ሰላማዊ መፍትሔ ሲያራምደው የነበረው ሐሳብ በገዢው ፓርቲና በመንግስትም ዘንድ በይፋ ይታወቅ እንደነበር፣ በመሆኑም በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች የተገለጸው ፈጽሞ ሐሰትና ትክክለኛ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

**4.2.8** በአጠቃላይ በእነዚህ ሁሉ የተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮችና ሰነዶች በተጨባጭ ሁኔታ የተረጋገጠው ግዙፍ ሐቅ ሁለታችንም ተከሣሾች በአገራችን የተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ በጽናት መስራትና መድከማችን እንጂ በማናቸውም መልኩ በሕገወጥና የአመጽ ተግባር ፈጽሞ የተሰማራን አለመሆኑ ነው።

**4.3 <u>የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 እና ምስክሮቹን በተመለከተ</u>**

**4.3.1** በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 ስር ተመዝግቦ ያቀረበው ሰነድ ኤልያስ ክፍሌ የተባሉ ሰው ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ኃይሌ ለተባሉ ሰዎች የጻፉት ደብዳቤ የተባለ ወረቀት ነው። እንዲሁም በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 65 ስር ተመዝግቦ የቀረበው ሰነድ አዳነ በቀለ የተባለው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ነፃነት ደምሴ ለሕዝብ እንድበትን የሰጠኝ ሰነድ ነው ያለው በራሪ ወረቀቶች ናቸው። በተለይ እነዚህ ሰነዶችና የዐቃቤ ሕግ ምክስሮች ፣ ሁለታችንን ተከሣሾች በሐሰት ለመወንጀል የተቀናበረውን ትያትር የሚያጋልጡ እንጂ ክሱን የሚያስረዱ እንዳልሆኑ እንደሚከተለው እናሳያለን።

**4.3.2** በኤልያስ ክፍሌ የተጻፈ ደብዳቤ ስለተባለው ሰነድ ጉዳይ በዚህ የክርክር መደምደሚያ ማመልከቻ በተራ ቁጥር 2.2.8 እና 2.2.9 ስር በአጭሩ ገልጸናል። የሰነዱ ፈጣሪዎች በተከሣሾችና እና በተቃዋሚው የፖለቲካ ፓርቲ መካከል ግንኙነት አለ ለማሰኘት ይረዳን ይሆናል ብለው ፈጥረው ያቀረቡት ሰነድ ነው። ይሁንና ይህ ሰነድ ፈጽሞ መሠረተ ቢስ እና የፈጠራ ስራ መሆኑ በብዙ መልኩ ተረጋግጧል። ከእነዚህም ዋናዎቹ፦

(ሀ) ሰነዱ ተጻፈ የተባለው ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃነ ኃይሌ ለተባሉ ሰዎች ሲሆን ተገኘ የተባለውም በእነዚሁ ሰዎች ቤት ነው። ሆኖም እነዚህ ሁለቱም ሰዎች ሰነዱ የእነርሱ መሆኑንና በቤታቸው መገኘቱን አላረጋገጡም። ብርሃነ ኃይሌ የተባሉት ሰው ቤት ተገኘ የተባለው ሰነድ ላይ «በእንግድነት ከአረፍኩበት ቤት የተገኘ በስመ ሞክሼ» የሚል ማስታወሻ ሰፍሮበታል ፣ ፍሬዘር ነጋሽ ቤት ተገኘ የተባለው ደግሞ ምንም ማረጋገጫ አልተሰጠበትም። በሁለቱም ቦታዎች በፖሊስ ተደረገ ስለተባለው የብርበራ ሁኔታ በዚህ የክርክር መደምደሚያ ማመልከቻ ከተራ ቁጥር 2.2.10 -

**2.2.12** ተገልጿል፡፡ እነዚህ ሰነዶች ተገኙ የተባሉበት ጠቅላላ ሒደቱ ምን ያህል ሕጋዊ አሰራርን ያልተከተለና ፈጽሞ አጠራጣሪ እንደነበር የዳኛ ሕሊና አይስተውም፡፡ በተለይም ከምስክሮቹ ውስጥ አቶ አዳሙ ለገሠ የተባሉት የዚህን ሰነድ ሁለተኛውን ገጽ እንደማያውቁት (ሁለተኛው ገጽ ስለ ተከሣሾች የተጠቀሰበት ነው) ለፍ/ቤት በሰጡት ምስክርነት አረጋግጠዋል፣

(ለ) ይህ ሰነድ ከአንድም ሁለት ቦታ ተገኝቷል ቢባልም ለፍርድ ቤቱ በማስረጃነት የቀረበው በፍተሻ ተገኝቷል የተባለው ዋና ሰነድ ሳይሆን፤ ፎቶ ኮፒ የሆነ ወረቀት ነው፡፡ ከዚህም በላይ ልክ ዋናው ሰነድ እንደቀረበና እንደታየ በማስመሰል ፈጽሞ ተገቢ ባልሆነ አሰራር ከዋናው ጋር የተመሳከረ በማስመሰል በሬጅስትራር ጽ/ቤት ማህተም ታትሞ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም ይህ ተገቢ ያልሆነ አሰራር ተከሣሾች በአደረግነው ማጣራት በመታወቁ ፍርድ ቤቱም አሰራሩ ትክክል አለመሆኑን ገልጿል ፣ ይህም ሰነዱ ትክክለኛ እና እውነተኛ (authentic and genuine) እንዳልሆነ ያረጋግጣል፣

(ሐ) ይህን ደብዳቤ ጽፈዋል የተባሉትንም ሰው ሆነ ደብዳቤው ተጻፈላቸው የተባሉትን ሰዎች እኛ ሁለታችንም ተከሣሾች ፈጽሞ አናውቃቸውም፣ ከእኛም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አላቸው ተብሎ የተገለጸ ነገር የለም ፤ ሊኖርም አይችልም፡፡ ሰነዱ ማንም ሰው ሊጽፈው እንደሚችል በኰምፒዩተር የተጻፈ ሁለት ገጽ ወረቀት ሲሆን የማንም ሰው ፊርማ የሌለው፣ የማን እንደሆነ አንዳችም ማረጋገጫ የሌለው ወረቀት ነው፣

(መ) በዚህ ሰነድ ላይ የተጻፈው ኤልያስ ክፍሌ የተባሉ ሰው ከአቶ ኃይሉ ሻውል በተነገራቸው መሠረት ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ የቅንጅት ፓርቲ አገናኝ መኮንኖች (contact persons) ናቸው የሚል ነው፡፡ ሁለታችንም ተከሣሾች የደብዳቤውን ጸሐፊም ሆነ ተጻፈላቸው የተባሉትን ሰዎች ሳናውቃቸው ወይም ከእነሱ ጋር ግንኙነት አላቸው እንኳን ሳይባል ፤ አንድ እኛ የማናውቀው ሰው ለሌሎች እኛ ለማናውቃቸው ሰዎች ጽፈዋል በተባለው ደብዳቤ ሌላ ሶስተኛ ሰው እንዲህ ብሏል ተብሎ የተገለጸ በመሆኑ የሰሚ ሰሚ (hearsay) ብቻ ሳይሆን የሰሚ ሰሚ ሰሚ (more than a hearsay) የሆነ በየትኛውም መስፈርት ዋጋ ሊሰጠው የማይችል ወረቀት ነው፡፡

(ሠ) ከዚህም ሁሉ በተጨማሪ በዚህ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ሰነድ ላይ የተጻፈው ፈጽሞ ሐሰት ስለመሆኑ የተከሣሾች መከላከያ ምስክሮች ለፍርድ ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል አረጋግጠዋል፡፡ ይኸውም፡-

- በሰነዱ የተገለጸውን ተናግረዋል የተባሉት የቅንጅት ፓርቲ ሊቀመንበርና 2ኛ መከላከያ ምስክር ኢ/ር ኃይሉ ሻውል በሰነዱ የተጻፈውን ቃል ፈጽሞ እንዳልተናገሩ፣ ኤልያስ ክፍሌ ከተባለውም ሰው ጋር ድርጅታዊ ግንኙነት እንዳልነበራቸው፣ ሁለታችንንም ተከሣሾች የቅንጅት ፓርቲ አገናኝ መኮንን ናቸው የተባለው ትክክል አለመሆኑንና ይልቁንም ተከሣሾችን የሚያውቁት ከዚህ በአንድነት ከቀረበባቸው ክስ በኋላ መሆኑን አረጋግጠዋል፣
- ሌሎች የቅንጅት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አባሎችም ውስጥ 75ኛ ምስክር ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም፣ 118ኛ ምስክር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው፣ 151ኛ ምስክር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ እና 153ኛ ምስክር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በተመሳሳይ መልኩ ተከሣሾች የቅንጅት ፓርቲ አገናኝ መኮንኖች ናቸው የተባለው ትክክል አለመሆኑና ተከሣሾች ከፓርቲው ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው አረጋግጠዋል፡፡
- ይህን ጭብጥ በሚመለከት የቀረቡት የተከሣሽ መከላከያ ምስክሮች በሚመለከት ዐቃቤ ሕግ የሰጠው አስተያየት አንዳችም ሕጋዊ መሠረት የለውም፡፡ እነዚህ ምስክሮች ተከሣሾች የነበሩ መሆኑ የሚያውቁትን ከመመስከር አይገድባቸውም፡፡ ምስክርነት የሰጡበትም ቀጥተኛና ግልጽ ሲሆን፤ በጭብጡ መሠረት ሁለታችን ተከሳሾች የቅንጅት ፓርቲ አገናኝ መኮንኖች ናቸው የተባለው ትክክል አለመሆኑን አረጋግጠው መስክረዋል፡፡

## 4.4 <u>የዐቃቤ ሕግ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 65 እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን በተመለከተ (አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዩም) በተመለከተ</u>

4.4.1 በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ሰነድ ማስረጃ ቁጥር 65 ስር ተመዝግቦ የቀረበውና አዳነ በቀለ የተባለው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ነፃነት ደምሴ የሰጠኝ ወረቀቶች ናቸው በማለት የቀረቡት ሦስት ገጽ ወረቀቶችም ሌላው አሳዛኝ የፈጠራ ስራ ነው፡፡ እነዚህ ወረቀቶች በየጋዜጣው፣ በኢንተርኔትና በልዩ ልዩ ሬድዮኖች በገዢው ፓርቲና አመራሮቹ ላይ የሚወሩትን ወሬዎች በኮምፒዩተር በሦስት ገጾች ተጽፈው የቀረቡ ሲሆን ፤ እነዚህን ወረቀቶች

ለሕዝብ እንድበትን የሰጠኝ ነፃነት ደምሴ ነው በማለትና የነገሩ ብቸኛ ምስክር ነኝ በማለት የቀረበው አዳነ በቀለ የሚባለው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ነው::

4.4.2 ከዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ውስጥ አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዩም የተባሉት ምስክሮች የሰጡትን ቃል በተራ ቁጥር 2.2.6 እና 2.2.7 ስር ገልጸናል:: እነዚህን ሁለቱንም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ፈጽሞ አይቼ እንኳን የማላውቃቸው ሰዎች ናቸው:: 95ኛው ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ፣ አዳነ በቀለ የሚባለውን የዐቃቤ ሕግ ምስክር በጉርብትና ደረጃ ብቻ ያውቀዋል:: ከጉርብትናቸው ውጪ ምንም ግንኙነት የላቸውም:: የእነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ፈጽሞ የማይታመንና ሐሰት ስለመሆኑ ለማስረዳት ከምስክርነት ቃላቸው የሚከተለውን ለአብነት ያህል እንጠቅሳለን፣ በአንጻሩም ፍ/ቤቱ ስለ ሁለታችንም ተከሣሾች ተግባርና ምግባር በምስክርም በሰነድም ከቀረበው መከላከያ ማስረጃ አንጻር እንዲመዝነው እንጠይቃለን::

(ሀ) ሁለቱም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ በነገሩን መሠረት ሕዝቡን ለአመጽ ቀሰቀስን አደራጀን ይበሉ እንጂ ፣ ሁለቱም ምስክሮች የተናገሩትንና አደረግን የሚሉትን ነገር በሙሉ ሁለቱም በየበኩላቸው ከእራሳቸው ውጪ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም ማለታቸው፣

(ለ) ሁለቱም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የአካባቢያችን ሰዎችን ቀሰቀስን አደራጀን ይበሉ እንጂ ቀሰቀስን ወይም አደራጀን ከሚሏቸው ሰዎች ውስጥ የአንድ ሰው እንኳን ስም አናውቅም ማለታቸው፣

(ሐ) በየመንገዱ፣ በየታክሲው እና በቡና ቤት ውስጥ የማናውቀውን ሰው ሁሉ እያናገርን፣ እዚያው መንገድ ላይ እና ቡና ቤት ውስጥ እያሳመንን ቀስቅሰን አደራጀናቸው ማለታቸው፣

(መ) አዳነ በቀለ የተባለው ምስክር በአንድ ቀን አንድ ቡና ቤት ውስጥ ገብቼ 15 ሰው ከዚያም በላይ ሰዎች አነጋግሬ አሳምናቸውና ለአመጽ ዝግጁ አደርጋቸዋለሁ ማለቱ፣

(ሠ) አዳነ በቀለ የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን አገኘሁ የሚለው ለሦስት ቀን ሲሆን ፤ በመጀመሪያ ጊዜ ለ10-15 ደቂቃ፣ ሁለተኛውና ሦስተኛው ጊዜ በድንገት በመንገድ ላይ ሲሆን ፤ ሕዝቡን ለአመጽ ስለመቀስቀስና ማደራጀት መመሪያ ሰጠኝ የሚለው በዚሁ ግዜ መሆኑን መግለጹ፣

(ረ) ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን አገኘሁ የሚለው ለሁለት ቀን ሲሆን ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በአጋጣሚ ሁኔታ ለ2 (ሁለት) ደቂቃ ብቻ በሁለተኛው ጊዜ ደግሞ መንገድ ላይ ሲሆን ፤ ሕዝቡን ለአመጽ ስለመቀስቀስና ማደራጀት መመሪያ ሰጠኝ የሚለው በዚሁ ግዜ መሆኑን መግለጹ፣

(ሰ) ሁለቱም ምስክሮች ተሰውረን ቆይተን በኋላ ለፖሊስ እጃችንን ሰጠን ያሉ ሲሆን ፤ ሁለቱም ከቤተሰባቸው ውስጥ ይህን ሁኔታ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም፣ ያነጋገርነውን ፖሊስ ስም አናውቅም፣ በአጠቃላይ ስለ ተናገሩት ነገር ሁሉ ከእራሳቸው ውጪ አንድም የሚያውቅ ሰው የለም ማለታቸው፣

(ሸ) በተለይ አዳነ በቀለ የተባለው ምስክር 25 ዓመት ኖሬበታለሁ፣ በቀበሌ ጽ/ቤት ውስጥ የአመራር አባል ነበርኩ በሚልበት አካባቢ ፤ የአካባቢውን ሰው ሁሉ ቀሰቀስኩ አደራጀሁ እያለ የአንድ ሰው ስም እንኳን አላውቅም ማለቱ፣ በሰፈሩ ጓደኞቼ ለሚላቸው ሰዎችም እንኳን ስለ አንዱም ነገር ለየትኛውም ሰው አልነገርኩም ማለቱ፣

(ቀ) አዳነ በቀለ የተባለው ምስክር ነፃነት ደምሴ ሰጥቶኛል የሚለውን ወረቀት ለእነማን እንደሰጠ ሲጠየቅ ለማላውቃቸው ሰዎች ታክሲ ውስጥ ሰጠሁኝ ማለቱ፣

(በ) ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን ማንም ሰው ሳያስተዋውቀኝ ሻይ ቤት ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር ሳወራ የነበረውን ሰምቶ እራሱ መጥቶ ተዋወቀኝ ፤ ከዚያም ሕዝቡን ለአመጽ ስለመቀስቀስና ማደራጀት ነግሮኝ በዚሁ መሠረት ሰርቻለሁ በማለት መግለጹ፣

(ተ) ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን ቀደም ሲል አላውቀውም፣ በአጋጣሚ ሻይ ቤት በር ላይ ተዋውቀው በግምት ለሁለት ደቂቃ አነጋገርኩት፤ በዚሁ በሁለት ደቂቃ ትውውቅና ግዜ ሕዝብን ለአመጽ ስለማደራጀት መንግስት ስለመገልበጥ መመሪያ ሰጥቶኛል፣ ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ መንገድ ላይ ተቀጣጥረን በመንገዱ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተነጋግረናል በማለት መግለጹ፣

(ቸ) ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን ለሁለተኛ ጊዜ እንዴት እንዳገኘው ተጠይቆ ሲመልስ ፤ ቢሮው ድረስ ሄጄ ዳንኤል እዚህ ነው ወይ ብዬ ጠይቂ አገኘሁት፣ በሱቅ ስልክ ሚስድ ኮል (missed call) አድርጌለት አገኘሁት፣ ሚስድ ኮል አደረኩኝ እንጂ አላነጋገርኩትም፣ ቢሮው ሳይሆን ወደ ቢሮው መግቢያ መንገድ ላይ አገኘሁት፣ ስልክ ደውዬ አናግሬው መንገድ ላይ ተቀጣጥረን አገኘሁት፣ . . . ወዘተ የሚል እርስ በእርሱ የሚቃረን ቃል መናገሩ፣

(ኀ) ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለ ሕዝቡን ለአመጽ ለማደራጃ 200 ብር ሰጥቶኝ በዚሁ መሠረት አደራጀሁበት፣ የአደራጀሁትን ሰዎች የአንዱንም ስማቸውን አላውቅም ማለቱ፣ መንገደኛውን ሰው ሁሉ እያስቆምኩኝ ለውጥ አትፈልጉም ወይ ለውጥ እናምጣ እያልኩኝ በመናገር መንገደኛውም ለውጥ ስለሚፈልግ እሺ እያለኝ አደራጀው ነበር ማለቱ፣

(ነ) ይኸው ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ከዚህ ድርጊት በኋላ ተሰውሬ በአንድ ሰዎች ቤት ተደብቄ ነበር ካለ በኋላ በዚህ ተሰወርኩ ባለበት ጊዜ ተደብቄ ነበር የሚልባቸው ሰዎች ስም ሲጠየቅ አላውቃቸውም ማለቱ፣ የቦታውን አድራሻ በትክክል እንዲገልጽ ሲጠየቅም አድራሻውንም አላውቀውም ማለቱ፣

(ኘ) ይኸው ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር የኢዴአፓ ፓርቲ አባል ነኝ በማለት የገለጸ ሲሆን ፤ ከዳንኤል በቀለ ጋር በድንገት ተገናኝቼና ተዋውቄ አደረኩኝ ስለሚለው ነገር በሙሉ አባል ነኝ ለሚልበት ፖለቲካ ፓርቲ አሳውቆ እንደሆነ ሲጠየቅ ፤ ለማንም ሰው

አልተናገርኩም ማለቱ፣ በአጠቃላይ ከዳንኤል በቀለ ጋር ነበረኝ ስለሚለው ግንኙነት ሌላ የሚያውቅ ወይም የነገርኩት አንድም ሰው የለም በማለት መግለጹ፣

(ለ) ይኸው ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ዳንኤል በቀለን ያየሁት ለሁለት ቀን ብቻ ነው፣ በአጋጣሚ ከመተዋወቃችን በፊት አላውቀውም ካለ በኋላ ፤ እንደገና ደግሞ «ዳንኤልን አንድ ቀን ታምራት ቢሮ አይቼዋለሁ፣ ከታምራት ጋር መንገድ ላይ ቆሞ አይቼዋለሁ፣ ሳንተዋወቅ በፊት ነበር፣ በዚያን ጊዜ ተዋውቀናል፣ ከታምራት ጋር መንገድ ላይ ቆመው ያየሁት እኔ ዳንኤልን ሻይ ቤት ከማግኘቴ በፊት ነው፣ . . .» ወዘተ የሚል እርስ በእርሱ የሚቃረን ቃል መስጠቱ፣ (በሐሰት እንዲመሰክር ተፈልጎ የነበረው ዳንኤል በቀለን ከሌላው ተከሣሽ ከታምራት ታረቀኝ ጋር አይቼው አውቃለሁ እንዲል ነበር፡፡ ታምራት ታረቀኝ ከቅንጅት ፓርቲ ተከሣሾች አንዱ ሲሆኑ እኔ ዳንኤል በቀለ እኚህን ሰው ከመታሰሬ በፊት አይቼም እንኳን አላውቃቸውም ፤ የዐቃቤ ሕግ ምስክሩም አጥንቶ የመጣው ታሪክ ተደባልቆበት እርስ በእርሱ የሚቃረን ቃል ሰጥቷል፡፡ አቶ ታምራት ታረቀኝም በተከሣሾች 140ኛ መከላከያ ምስክርነት ቀርበው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለን በዚህ በአንድነት ከተያዙበትና በተከሰሱበት ጉዳይ በፊት ፈጽሞ እንደማያውቁት አረጋግጠዋል፡፡) ዐቃቤ ሕግ የራሱ ምስክር በሰጡት በዚህ የሚቃረን ቃል ላይ በሰጠው አስተያየት «…በአጋጣሚ በመመሳሰል ያየው መስሏቸው ሊሆን ይችላል…»በማለት ነገሩን ይበልጥ አስቂኝ አድርጎታል፡፡

(ከ) ይኸው ወንድወሰን ስዩም የተባለው ምስክር ለፖሊስ አንድ ጊዜ የተከሳሽነት ቃል ሰጥቻለሁ፣ ሌላ ጊዜ የምስክርነት ቃል ሰጥቻለሁ በማለት የተምታታ ቃል ሲናገር ቆይቶ ፤ በመጨረሻ በዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ደግሞ ፖሊስ ዘንድ ቀርቤ ቃል የሰጠሁት አንድ ጊዜ ብቻ ነው በማለት መግለጹ፣

(ኸ) አዳነ በቀለ የተባለው ምስክር በጥቅም ተደልዬ ሕገወጥ ስራ እሰራ ነበር በማለት የተናገረ ስለሆነ ፤ አሁንም በጥቅም ተደልሎ በሐሰት

ሊመሰክር የሚችል ሰው እንደሆነ የሚያረጋግጥ መሆኑንና ፣ በእርግጥም ይኸው በተግባር መታየቱ፣

(ወ) ከ95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ጋር በአንድ አካባቢና በጉርብትና ለረጅም ጊዜ የኖሩ የተከሣሾች መከላከያ ምስክሮች ውስጥ 15ኛው ምስክር አቶ ተካልኝ ቶሎሳ፣ 17ኛው ምስክር አቶ ተሰማ አባተ እና 90ኛው ምስክር አቶ ስዩም ብርሃኑ በአንድ አይነት ቃል በሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ በአካባቢው በጨዋነቱና በሰላማዊነቱ የሚታወቅ፣ በአጠቃላይ የቤተሰብ አስተዳደጉም ከቤቱ ወደ ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ወደ ቤቱ ብቻ እንጂ ከሰፈር ልጆች ጋር የማያዘወትር መሆኑ፣ ወደ ስራ አለም ከገባም በኋላ በተመሳሳይ ባሕሪ የሚታወቅ እንጂ በአንዳችም መጥፎና ፀረ-ሰላም ተግባር የሚታወቅ አለመሆኑን እንዲሁም አዳነ በቀለ ከተባለው የዚያው ሰፈር ልጅ ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው፣ምግባራቸውም እንደማይገናኝ በማረጋገጥ መስክረዋል፡፡

(ዐ) አዳነ በቀለ የተባለው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 22 እና 23 ቀን 1998 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በነበረው አመጽ ነፃነት ደምሴ በወላጆቹ ቤት ሰፈር ውስጥ ሆኖ አመጹን እንዳስተባብርና እንድመራ ነግሮኛል በማለት የተናገረው ፈጽሞ በሐሰት የመሰከረው ስለመሆኑ በተከሣሾች 132ኛ ምስክር ሚ/ስ ማርያ ሆዜ ጌሬሮ በሰጡት ምስክርነት ተረጋግጧል፡፡ እኚህ የመከላከያ ምስክር በዚህ በተባለው ቀናት ጓደኛቸው ነፃነት ደምሴ ወላጆቹ ቤት ሳይሆን እርሳቸው ቤት አንድ ላይ እንደነበሩ፣ ሌሎች ጓደኞቻቸውም አብረው እንደነበሩ፣ በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ በተፈጠረው ሁከት የተነሳ የፀጥታ ስጋት ስለነበረ ወደ ስራ ሳይሄዱና ከቤትም ሳይወጡ ከነፃነት ደምሴ ጋር አብረው መቆየታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ዐቃቤ ሕግ እኚህ ምስክር በግልጽ ያስረዱትን ፍሬ ነገር እንደሚፈልገው በመተርጐም የሰጠው አስተያየት እጅግ አሳዛኝ ነው፡፡ ምስክሯ የሚያውቁትን ጉዳይ እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ አረጋግጠዋል፣ አንዳችም ቅራኔ የለውም፣ በጭብጡ መሠረት ተመስክሯል፡፡

(ዘ) ይኸው አዳነ በቀለ የተባለው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ፍጹም በሐሰት ነፃነት ደምሴ ሰጠኝ የሚለው ወረቀቶች በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ

ማስረጃ ቁጥር 20.1 ስር በናሙና ማስረጃነት በቀረበው የጋዜጣ ዘገባ ላይ እንደተመለከተው በወቅቱ በየጋዜጣውና የኢንተርኔት ድረ-ገጾች ይጻፍና ይወራ የነበረ ማንም ሰው እንደፈለገውና እንደተሰማው ሊጽፈው፣ ሊበትነው የሚችል የተለመደ የከተማ ወሬ ወይም አሉባልታ እንጂ ከዚህ የበለጠ ፋይዳ እንደሌለው የሚያረጋግጥ ነው።

4.4.3 ተከሣሾች ወጣቶችን በአመጽ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ገፋፍተዋል እንዲሁም ደግፈዋል የተባለውም ፈጽሞ ትክክል እንዳልሆነና ይልቁንም ተከሣሾች ከወጣቶችና ከወጣቶች ማህበሮች ጋር በነበረን የስራ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንሰራ እንደነበር፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በፀረ-ሰላምና በሕገወጥ ተግባር ላይ ፈጽሞ ያልተሳተፍን መሆኑን በመከላከያ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች አረጋግጠናል።

በተለይም በወጣቶች ማህበሮች አመራር አባልነታቸው በምርጫው ዘመን በ1997 ዓ.ም ከተከሣሾች ጋር የስራ ግንኙነት የነበራቸው ወጣቶች ውስጥ በተከሣሾች የመከላከያ ምስክርነት የቀረቡት 4ኛው ምስክር ወጣት ካሳሁን በለጠ እና 79ኛው ምስክር ወጣት ኢዮብ ባልቻ እንዲሁም የተከሣሾች የስራ ባልደረባ የሆኑት 123ኛ ው ምስክር አቶ ፍቅሬ ዘውዴ በሰጡት የምስክርነት ቃል እና በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃዎች ከዚህ በታች የተገለጹት አብይ ፍሬ ነገሮች በተጨባጭ ሁኔታ ተረጋግጠዋል፡-

(ሀ) ተከሣሾቹ በምስክሮቹ ከተገለጹት ከወጣቶች ማህበሮቹ ጋር ሙሉ በሙሉ ሕጋዊና ሰላማዊ የስራ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ

(ለ) በተለይም ከአክሽን ኤድ ድርጅት የፖሊሲ ሥራ አስኪያጅ ከነበረው 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ጋር ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ያገኙ እንደነበርና በዚህ የፋይናንስ እርዳታ ምክንያት በወጣቶች ማህበሮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማናቸውም ዓይነት ተጽእኖ ተደርጎባቸው እንደማያውቅ፣ ወጣቶችን ለህገወጥና ፀረ-ሰላም አላማ እንዲያነሳሱ ወይም ሌላ ማናቸውም ይህን የመሰለ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ማንኛውም ዓይነት ተጽእኖ ተደርጎባቸው እንደማያውቁ፣ ከተከሣሹ ጋር በነበራቸው የስራ ግንኙነትም ተገቢውን ድጋፍና እገዛ ከማግኘታቸው ውጪ በተከሣሽ ላይ ፀረ-ሰላም ወይም ሕገወጥ ተግባርና እንቅስቃሴ አይተው እንደማያውቁ፣

(ሐ) 79ኛው ምስክር ወጣት ኢዮብ ባልቻ አባል የሆነበት የወጣቶች ማህበር ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በአዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ በተጋባዥ እንግድነት ተገኝቶ ንግግር

ማደረጉንና በዚህም አንዳችም ፀረ-ሰላም ወይም ሕገወጥ የሆነ ንግግር ወይም ወጣቶችን የመቀስቀስ ተግባር አለመፈጸሙን፣

(L) ሁለታችንም ተከሣሾች ከወጣቶቹ ማህበራት ጋር ዓለም ዓቀፍ የፀረ ድሕነት ዘመቻ (Global Call for Action against Poverty) ላይ አብረን እንሰራ እንደነበርና በዚህ ስራ ላይም ተከሣሾች ሙሉ በሙሉ በሕጋዊና ሰላማዊ ተግባር ላይ ከመታየታችን በስተቀር አንዳችም ፀረ-ሰላም ወይም ሕገወጥ ተግባርና እንቅስቃሴ ያላደረግን መሆኑ፣

(P) በተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 19 ስር በናሙናነት ደረጃ በቀረቡ ሰነዶች እንደተመለከተው ተከሣሾች ከወጣቶችና ከወጣቶች ማህበሮች ጋር በሕግና በሥርዓት የተደገፈ ግንኙነት እንደነበራቸው የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ (የሰነድ ማስረጃዎቹ ስለሚያስረዱት ጭብጥ ዝርዝር መግለጫ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ ላይ ቀርቧል፡፡)

በአጠቃላይ እነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል ፈጽሞ ሐሰተኛ መሆናቸውንና ይልቁንም ተከሣሾችን በሐሰት ለመወንጀል የተቀናበረውን ድራማ የሚያጋልጥ ነው፡፡ ከዚህ በላይ እንደገለጽነው ፍርድ ቤቱ የእነዚህን ምስክሮች ቃል ስለ ተከሣሾች ተግባርና ምግባር ከቀረቡት የከበደ ግምት ሊሰጣቸው ከሚችሉት የመከላከያ ማስረጃዎች አንጻር እንዲመዝነው እንጠይቃለን፡፡

## 4.5 <u>የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች (መሠረት ወርቁ እና ንግስት መኳንንት) በተመለከተ</u>

4.5.1 ሁለቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎች የሆኑት ወ/ሮ መሠረት ወርቁ እና ወ/ሮ ንግስት መኳንንት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ምስክሮች በአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር አባልነታቸው እንደ ሥራ ጓደኞቻችን የምንቆጥራቸውና መልካም የሥራ ግንኙነትም የነበረን ሰዎች ናቸው፡፡ እኛ በቅን ልቡና ይህን እምነት ይዘን የኖርን ቢሆንም ሁለቱም ሰዎች እጅግ በሚያሳዝን መልኩ በሐሰት መስክረውብናል፡፡ ከእነዚሁ ሰዎችና ከሌሎችም የማህበራቸው አባሎች ጋር በጋራ ስናከናውን የነበሩትን እጅግ ጠቃሚ ስራዎች ዛሬ ጥላሸት እየቀቡት፣ ያልነበረውን ትርጉም እየሰጡት፣ ፈጽሞ ያላልነውን ነገር ተናገሩ፣ አደረጉ እያሉ በሐሰት ቢናገሩም ፣ ምስክርነታቸው ሊታመን የማይችል፣ ቅን ልቡና

የጐደለው፣ አሁን ለመረዳት እንደቻልነውም በግል ጥላቻና ቂም ላይ የተመሰረተ፣ የግል አስተያየታቸው እንጂ ተጨባጭ ፍሬነገር ያልሆነ እና በሁለታችን ተከሣሾች ላይ ከቀረበው ክስ አንጻር ብቃትም ሆነ አግባብነት የሌለው መሆኑን እንደሚከተለው እናሳያለን:: ለአብነት ያህል በእነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የተነገረው ውስጥ የሚከተለውን የምስክርነታቸውን ቃል እንጠቅሳለን፤ በአንጻሩም የተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮችና ሰነዶች የሚያስረዱትን ግዙፍ ሐቅ እናስረዳለን፤ ፍርድ ቤቱም ከዚህ በላይ እንደገለጽነው ስለ ተከሣሾች ተግባርና ምግባር ከቀረበው ማስረጃ አንጻር እንዲመዝነው እንጠይቃለን::

(ሀ) ወ/ሮ መሠረት ወርቁ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሰጡት ቃል የግል አስተያየታቸው መሆኑን እራሳቸው መግለጻቸው ፣

(ለ) እኚሁ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሁለታችን ተከሣሾች ሲናገሩ ሰምቻለሁ ስለሚሉት ነገር ማንኛችን እንደተናገርን ለይተው እንዲያስረዱ ለቀረበላቸው መስቀለኛና ማጣሪያ ጥያቄ ሲመልሱ አንድ ጊዜ ዳንኤል ነው፣ ሌላ ጊዜ ነፃነት ነው ሲሉ ቆይተው በመጨረሻ ደግሞ እኔ ሁለቱን ለይቼ አላውቃቸውም፣ ይምታቱብኛል፣ ግን ሁለቱም አንድ ናቸው፣ ሐሳባቸው አንድ ነው በማለት መናገራቸው፣

(ሐ) እኚሁ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የእርሳቸው ዋነኛ ቅሬታ ተከሣሾች የምርጫ ታዛቢዎችን በየምርጫ ጣቢያው ሲደለድሉ እርሳቸውን ከቤታቸው ራቅ ያለ ቦታ በመመደባቸው መሆኑን መግለጻቸው፣

(መ) እኚሁ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በተለይ ከፍ/ቤት በተደጋጋሚ ለቀረበላቸው የማጣሪያ ጥያቄ ሲመልሱ ፤ በእርግጥ ታዛቢዎችን የማሰማራት ኃላፊነት የተከሣሾቹ የነበረ ቢሆንም ፤ እርሳቸው ቤታቸው አቃቂ ቃሊቲ ሆኖ የተመደቡት ግን ልደታ አካባቢ በመሆኑ በጣም ቅር እንደተሰኙና ቅሬታቸውም ይኸው ብቻ እንጂ ከዚህ ውጪ ሌላ ነገር አለመሆኑን በግልጽ መናገራቸው ምስክርነታቸው ከግል ቅሬታና ጥላቻ የመነጨ መሆኑን ማረጋገጡ፣

(ሠ) እኚሁ ምስክር በአንድ በኩል በሲቪል ማህበሩ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎችን ስልጠና እየነቀፉ በሌላ በኩል የሲቪል ማህበር ታዛቢነት ስራቸውን በገለልተኝነትና በብቃት እንዲያከናውኑ ለሁለት ቀን ሙሉ የሰለጠኑበትን የታዛቢዎች ሥነ ምግባር ደንብ አላስታውሰውም፣ የታዛቢነቱን ሥራ ሳከናውንም አላስታውሰውም ነበር በማለት መግለጻቸው ስለ ምስክሯ ግምት ለመውሰድ የሚያስችል መሆኑ፣

(ረ) ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር በ94ኛ ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ላይ የአላቸውን ቅሬታና ቅያሜ መናገራቸው ምስክርነታቸው ከግል ቅሬታና ጥላቻ የመነጨ መሆኑን ማረጋገጡ፣

በአጠቃላይ የእነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ፣ ከቅን ልቡና ውጪ ፣ በግል ጥላቻና በሐሰት የተናገሩ መሆኑን በሚገባ የሚያረጋግጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በቀይ መስቀል የስብሰባ አዳራሽ ስለተካሄደው ሲቪል ማህበረሰቡ ስብሰባ የሰጡት የምስክርነት ቃል ትክክለኛ አለመሆኑ ከዚሕ በላይ ከተራ ቁጥር 4.2.2 እስከ 4.2.8 እንደተገለጸው በተጨባጭ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን፤ ከዚህ በታች ደግሞ ወ/ሮ መሰረት ወርቁ እና ወ/ሮ ንግስት መኳንንት ስለ ሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ስራ እንቅስቃሴና የተከሣሾች ተሳትፎ የሰጡት ምስክርነት ፈጽሞ ትክክል አለመሆኑ በተከሣሾች መከላከያ ምስክሮች መረጋገጡን እናስረዳለን::

4.5.2 እነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሲቪል ማህበረሱን የምርጫ መታዘብ እንቅስቃሴና የተከሳሾች ተሳትፎ በሚመለከት የሰጡት ፈጽሞ ትክክለኛ ያልሆነ ቃል ይታወሳል:: (ተራ ቁ. 2.2.4-2.2.5)

የሲቪል ማሕበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ስራ እንቅስቃሴና ሒደት ውስጥ ጉዳዩን በቅርብ ከሚያውቁና በልዩ ልዩ ደረጃ ተሳታፊዎች ከነበሩ ሰዎች ውስጥ በተከሣሾች የመከላከያ ምስክርነት ቀርበው የመሰከሩት 11ኛ ምስክር ሚ/ር ሪቻርድ ቼምበርስ፣ 59ኛ ምስክር ወ/ት ኢየሩሳሌም ተሾመ፣ 78ኛ ምስክር አቶ ደበበ ሀ/ገብርኤል፣ 89ኛ ምስክር ወ/ሮ ሳባ ገ/መድህን፣ 123ኛ ምስክር አቶ ፍቅሬ ዘውዴ፣ 125ኛ ምስክር ዶ/ር ቆንጂት ፈቃደ፣ 134ኛ ምስክር አቶ ማንያውቃል መኮንን እና 155ኛ ምስክር ወ/ት ብዙወርቅ ከተተ

በሰጡት የምስክርነት ቃል የተረጋገጠው ግዙፍ ሐቅ አብይ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:-

(ሀ) ተከሣሾች ተሳታፊ የነበሩበት የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ስራ ሒደት ሙሉ በሙሉ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ መከናወኑን፣

(ለ) በዚህ የስራ ሒደት ውስጥም የተከሣሾች ተሳትፎ ሕጋዊና ሰላማዊ እንደነበር፣

(ሐ) በተለይም በግሎባል ሆቴል፣ በኢትዮጵያ ሆቴል እና በ CRDA አዳራሽ ተደርገው በነበሩ ስብሰባዎችም ሆነ በሌሎች ማናቸውም ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይደረጉ በነበሩ ስብሰባዎች ተከሣሾች ሕገወጥ የሆነ፣ ፀረ-ሰላም የሆነ፣ ከፖለቲካ አንጻር ወገንተኛ የሆነ ንግግር ወይም እንቅስቃሴ ፈጽሞ አድርገን እንደማናውቅ፣

(መ) በተለይ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት በሶስቱ ስፍራዎች የተደረጉ ስብሰባዎችን በሚመለከት በግሎባል ሆቴል እና በ CRDA አዳራሽ ስብሰባ ላይ ወ/ሮ መሠረት ወርቁ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተከሣሾች ተናግረዋል ያሉት በሙሉ ፈጽሞ ያልተባለና ያልተነገረ መሆኑንና እንዲያውም በግሎባል ሆቴሉ ስብሰባ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ፈጽሞ ያልነበረ መሆኑ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሆቴል ስለተደረገው ስብሰባ ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር የተናገሩት ትክክል አለመሆኑ መረጋገጡ፣

(ሠ) ተከሣሾች ተሳታፊ የነበሩበት የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ስራ እንቅስቃሴና ሒደት በከፍተኛ ሁኔታ የሙያ ደረጃውን የጠበቀ፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ እና ገለልተኛ በመሆን እንዲሁም በግልጽነት መርሕ መሠረት መከናወኑን፣

(ረ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የውጭ አማካሪ የነበሩት 11ኛው ምስክር ሚ/ር ሪቻርድ ቼምበርስ በሰጡት የምስክርነት ቃል በተለይ በስራቸው ምክንያት ከ95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ጋር በምርጫው ወቅት በቅርብ ለመገናኘትና ለመስራት እድል የነበራቸው በመሆኑ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴውንና የነፃነት ደምሴንም ተሳትፎ በቅርብ ለማስተዋል እንደቻሉና ከዚህም የተነሳ አጠቃላይ የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ እንቅስቃሴና ነፃነት ደምሴ በዚህ ውስጥ የነበረው ሚና ፍጹም የሙያ ደረጃን የጠበቀ፣ ሕጋዊ አሰራርን የተከተለ፣ በሰላማዊ መንገድ የተካሔደ እና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ የነበረ መሆኑን በሙሉ ስሜት ማረጋገጣቸው፣

(ሰ) በአጠቃላይ ወ/ሮ መሠረት ወርቁ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር በጠቀሱት የግሎባል ሆቴልና የ CRDA ስብሰባ እንዲሁም ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር በጠቀሱት የኢትዮጵያ ሆቴል ስብሰባ ጨምሮ በሌሎችም የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ጉዳይ ስብሰባዎችም ሆነ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች፤ ሁለታችንም ተከሣሾች የነበረንን ተሳትፎ ሕጋዊና ሰላማዊ እንደነበረ፣ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የገለጹትን አይነት ንግግር አድርገን እንደማናውቅ፣ ኃላፊነታችንን በተገቢው መንገድ ስንወጣ የነበርን ዜጐች መሆናችን እጅግ የከበደ ግምት ሊሰጠው በሚችል የተከሣሾች መከላከያ ምስክሮች ተረጋግጧል።

4.5.3 ከዚህ በተጨማሪም ከተራ ቁጥር 3 እስከ 16 ተመዝግበው የቀረቡ የተከሣሾች የሰነድ መከላከያ ማስረጃዎች ልክ በምስክሮቹ በተነገረው ዓይነት ተከሣሾች ተሳታፊ የነበሩበት የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ መታዘብ ስራ እንቅስቃሴና ሒደት ሐሳቡ ከተፀነሰበት የጥናት ፅሑፍና የመጀመሪያው የምክክር ስብሰባ አንስቶ እስከ መጨረሻው ቀን ያለው ተግባር በአጠቃላይ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ፣ በከፍተኛ ሁኔታ የሙያውን ደረጃ በጠበቀ ብቃትና ጥንቃቄ፣ በግልጽነት መርህ፣ እና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ በመሆን በገለልተኝነት መርሕ በመመራት መከናወኑን በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ናቸው። (እያንዳንዳቸው የሰነድ ማስረጃዎቹ ስለሚያስረዱት ጭብጥ ዝርዝር መግለጫ ሐምሌ 26 ቀን 1999 በተጻፈው የሰነድ ማስረጃዎች መግለጫ ላይ ቀርቧል።)

4.5.4 ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች እንኳንስ እንደ ክስ አቀራረቡ ሊያስረዱ ይቅርና ፤ ይልቁንም ክሱ ፈጽሞ ያለአግባብ የቀረበ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 መሠረት እንደሚታወቀው አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ (Legal elements)፣ ግዙፋዊ (Material elements) እና ሞራላዊ (Moral/State of mind) ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 238/258 በመተላለፍ ሕገመንግሥቱንና ሥርዓቱን ለማፍረስ በአድማ የሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአቀረበው ክስ ፤ ልክ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ስለ ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች በተደነገገው ዓይነት እና ስለ ሞራላዊ ፍሬ ነገርም

በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ በተደነገገው ዓይነት በማያጠራጥር ማስረጃ ክሱን እንዲያስረዳ ይጠበቅበት ነበር፡፡

4.5.5 ዐቃቤ ሕግ ተፈጽሟል የሚለውን ወንጀል የሚያቋቁሙት ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች በአንቀጽ 238/258 የተመለከቱት ሲሆኑ ሞራላዊ ፍሬ ነገርን በሚመለከት ደግሞ በአንቀጽ 58 በተመለከተው ዓይነት ሆነ ተብሎ ታስቦ (intentionally) የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ (ዐቃቤ ሕግ ተፈጽሟል የሚለው የወንጀል ተግባር ቸልተኝነትን የሚመለከት ስላልሆነ አንቀጽ 59 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው መሆኑ ይታወቃል፡፡)
የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በሙሉ በተናጠልም ሆነ በአንድነት ቢታዩ ከዚህ በላይ በተመለከተው አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ወንጀልን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን ለማስረዳት ብቃት የሌለውና ሊታመን የማይችል መሆኑን በተከሣሾች መከላከያ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡
ሁለታችንም ተከሣሾች እንኳንስ ሕገመንግሥቱንና ሥርዓቱን ሆነ ብለን አስበን በኃይል፣ በዛቻ በአድማ ወይም በሌላ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማፍረስ ሞክረዋል ልንባል ይቅርና ፤ ይልቁንም ተጨባጭ በሆነ ማስረጃ እንደተረጋገጠው ለሕገመንግሥታዊ አሠራር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረግን ዜጐች ነን፡፡

4.5.6 ከዚህ በላይ እንደገለጽነው አገራችን በአስጨናቂ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ በምትገኝበት ወቅት ሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርዱ የተረጋገጡላቸውን ወንበሮች ተረክበው ወደ ፓርላማ እንዲገቡና በሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ መሠረት ሥልጣን የሚረከበው መንግሥት እንዲመሠረት፣ ቅሬታ ያስነሱ የምርጫ ውጤቶች በፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲወሰኑ ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኃላፊነት ስሜት የፖለቲካ ውጥረቱን በማርገብ በሕግ፣ በሥርዓት፣ በሰላም፣ በሐቀኝነትና በቅንነት ለአገርና ለሕዝብ በማሰብ በጋራ ማሰብ፣ በጋራ ማቀድ እና በጋራ መስራት ይጀምሩ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከጥላቻ ንግግሮች ይታቀቡ፣.... ወዘተ የሚል ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ዓላማ በይፋ ይዘን ስንደክም የነበርን ዜጎች እንዴት ሆነ ብለውና አስበው ሕገመንግሥታዊ ሥርዓትን በኃይል፣ በዛቻ፣ በአድማ በሕገወጥ መንገድ ለማፍረስ ሲሞክሩ ነበር ተብለን ለመከሰስ እንበቃለን?

## 4.6 የሲቪል ማህበረሰቡን እንቅስቃሴና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን በተመለከተ

4.6.1 ዐቃቤ ሕግ በሁለታችን ተከሣሾች ላይ በአቀረበው ክስ ተከሣሾች የሚወክሉትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከመሠረታዊ ዓላማው ውጪ አንቀሳቅሰው ፖለቲካዊ ሥራ እንዲሰራ አድርገዋል በማለት ገልጿል::

4.6.2 በክሱ ውስጥ የተነሱትና በሲቪል ማህበረሰቡ የተከናወኑ ስራዎች አንደኛው የምርጫ መታዘብ ሥራ (Election Monitoring) ሲሆን ሁለተኛው የሲቪል ማህበረሰቡ የሰላም ጥሪት እንቅስቃሴ (CSOs Peace Plan Initiative) ነው:: እነዚህ ሁለቱም ስራዎች በአገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የተለመዱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተግባሮች ናቸው:: በአገራችን የቅርብ አስርት ዓመታት ታሪክ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በስፋት ይታወቁ የነበረው በዘይትና ዱቄት እርዳታ የነበረ ቢሆንም ፤ ይሄ የቀድሞ ታሪክ እንጂ ዛሬ የሲቪል ማህበረሰቡ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ንቁ ተሳታፊ ነው::

4.6.3 በእርግጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው:: ይህም ማለት እንደ ፖለቲካ ፓርቲ የመንግሥት የፖለቲካ ስልጣን መጨበጥ አላማቸው አይደለም ማለት ነው:: ከዚህ ውጪ ግን በአገራችንም ሆነ በመላው ዓለም ፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አበይት አላማዎች ሁሉ ተሳታፊዎች ናቸው:-

- መልካም አስተዳደርና ሰብዓዊ መብቶችን ማስፋፋት (Promotion of Human Rights and Good Governance)
- ግጭቶችን ማስወገድና ሰላም መገንባት (Conflict Prevention, Resolution and Peace Building) እና
- የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ (Democracy Building) ::

4.6.4. በአገራችንም በሕገመንግስት በተረጋገጠ መብት መሠረት እና መንግስትም በፖሊሲ ሰነዶቹ በግልጽ ባሰፈረው መሠረት የአገራችን ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በእነዚህና ሌሎችም ሰፊ ሰላማዊና ሕጋዊ ተግባሮች ይሳተፋሉ፣ እንዲሳተፉም ይበረታታሉ:: ትክክለኛው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ ፤ የአገራችን

ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የአከናወኑትን ተግባራት እንደማይፈቀድ የፖለቲካ ስራ አድርጎ መውሰዱ ስህተት ነው::

በተለይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምርጫውን የመታዘብ መብታቸው ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መሰናክል ገጥሞት ሲቪል ማህበረሰቡ መብቱን ለማስከበር በፍርድ ቤት በአቀረበው ክስ ምርጫውን የመታዘብ መብታቸው በፌዴራሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች የተረጋገጠ መሆኑ እየታወቀ ፤ ዛሬም እንደገና ይህ የሲቪል ማህበረሰቡ ሕጋዊና ሰላማዊ ስራ እንደማይፈቀድ ፖለቲካዊ ስራ መታሰቡ ስህተት ነው::

በግንቦት 97 ምርጫ ታሪካዊ የነበረውን የፖለቲካ ፓርቲዎች የክርክር መድረክ ያዘጋጁትና የመሩት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንደነበሩም የሚታወቅ ነው:: ይህ በጠባዩና በይዘቱ ፖለቲካዊ የሆነ ሆኖም የሚመሰገን የሲቪል ማህበሮች ተግባር እንጂ ፖለቲካዊ ስለሆነ ለሲቪል ማህበሮች የተከለከለ ስራ አይደለም::

4.6.5 የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ የተፈጠረው የፖለቲካ ግጭትና አጣብቂኝ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈታ የሲቪል ማህበረሰቡ የአደረገው እንቅስቃሴም በአገራችንም ሆነ በመላው ዓለም የታወቀ የተለመደ እጅግ የሚበረታታ የሲቪል ማህበረሰብ የሥራ ዘርፍ ነው::

የሲቪል ማህበረሰቡ ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. ያወጣው የሰላም ጥሪ ዝርዝሩ በዚህ የክርክር መደምደሚያ ማመልከቻ በተራ ቁጥር 4.1.5 ስር ተገልጿል:: ይህ የሰላም ጥሪ ሰነድ ሕጋዊና ሰላማዊ የመፍትሔ ሐሳብ እንደነበር እጅግ ግልጽ ነው:: ሲቪል ማህበረሰቡ ነፃና ገለልተኛነቱ ጠፍቶ ለምን አንደኛውን ወገን ብቻ አልደገፈም ካልተባለ በስተቀር ፤ ብዙ ታዛቢዎች እንደሚስማሙበት በሲቪል ማህበረሰቡ የቀረበው የሰላም ጥሪ በሁሉም ወገን ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ፤ ምናልባትም የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ የተከሰተው አሳዛኝ ሁኔታ ባልተፈጠረ ነበር::

4.6.6 በተመሳሳይ ሁኔታ የሲቪል ማህበረሰቡ ስለአከናወነው የምርጫ መታዘብ ስራ በመንግስት ከፍተኛ እውቅና የተሰጠው የካርተር ማዕከል እ.ኤ.አ. በሴፕ ቴምበር 2005 በአወጣው ሪፖርት የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል:-

> «. . . ምርጫ ቦርድ የተለያዩ አላስፈላጊ መስፈርቶችን በአገር ውስጥ ታዛቢዎች ላይ አውጥቷል:: በምርጫው ዋዜማ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ምርጫ ቦርድ ያወጣውን መመሪያ በማንሳት ለመታዘብ

ችለዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የተደረገው የአገር ውስጥ ታዛቢዎች መታዘብ በማይችሉበት፣ ታዛቢዎቻቸውን ማንቀሳቀስ በማይችሉበት በመጨረሻው ሰዓት ነው፡፡ የአገር ውስጥ ታዛቢዎች በብዛት ቢሳተፉ ኖሮ የቀረቡት ቅሬታዎች በቀነሱና የደረሱት አደጋዎችና ግራ መጋባቶች ባልተከሰቱም ነበር» በማለት ገልጿል፡፡

(የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ቁጥር 16.1 የካርተር ማዕከል ሴኘቴምበር 2005 ሪፖርት ገጽ 4 )

4.6.7 በአጠቃላይ ሁለታችንም ተከሣሾች ተሳታፊ የነበርንበት ሲቪል ማህበረሰቡ የአከናወነው ተግባሮች በሙሉ ሕጋዊ ፣ ሰላማዊና የተፈቀዱ ተግባሮች እንጂ ፤ የሲቪል ማህበረሰቡ አንዳችም ከመሰረታዊ ዓላማው ውጪ ሰርቷል የሚያሰኝ ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል በሲቪል ማህበረሰቡ የቀረበው የሰላም ጥሪ የሲቪል ማህበረሰቡ እንጂ የዳንኤልና የነፃነት የግል ጽሑፍ አይደለም፡፡ ከብዙ የስራ ጓደኞቻችን ጋር በአንድነት ተሳታፊ የነበርንበት የጋራ ስራዎች እንጂ የሁለት ሰዎች የግል ጉዳይ ወይም የግል ስራ አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሲቪል ማህበረሰቡ ያቀረበው የሰላም ጥሪ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ እንደምታ አለው የሚል የሰዎች አስተያየት ቢኖር፤ በሰነዱ የተገለጸው ሐሳብ እና ስለሰነዱ የሚሰጡ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ አስተያየቶች በሙሉ፤ ሐሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለጽ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብት መገለጫዎች ናቸው፡፡ በሰነዱ የተገለጸው ሃሳብ አሉታዊ ስሜት አለው የሚል አስተያየት መኖሩ፣ ሰነዱን ወንጀል አያደርገውም ወይም ሃሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለጽ መብትን አይገድብም፡፡

4.6.8 በተመሳሳይ መልኩ ወ/ሮ መሠረት ወርቁ እና ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ በስብሰባ ላይ ተናገሩ ያሉት ነገር በሙሉ በፍጹም በሐሰት የመሰከሩት ቢሆንም፤ በመሠረቱ ግን ተናገሩ የተባልነውን ነገር ተናግረንም ቢሆን ኖሮ ሃሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለጽ መብት ስር የሚታይ ነው፡፡

እንደ ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹ አባባል ተከሣሾቹ በስብሰባ ላይ ተናገሩ የተባለው «... ምርጫው ተጭበርብሯል፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም፣ የጥምር መንግስት ይቋቋም » የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ እንደገለጽነውና በተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮችም በበቂ ሁኔታ እንደተረጋገጠው የዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹ የሰጡት የምስክርነት ቃል ትክክለኛ አለመሆኑ የተረጋገጠ

ቢሆንም፣ በመሠረቱ ግን ይህን ተከሣሾች ተናገሩ የተባለውን ነገር መናገር በየትኛውም መስፈርት ወንጀል አይደለም::
ማንኛውም ሰው ስለ ምርጫው መጭበርበር ወይም አለመጭበርበር፣ ስለ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ መሆን ወይም አለመሆን፣ ስለ ጥምር መንግስት መቋቋም ወይም አለመቋቋም የመሰለውን ሐሳብ የመያዝ፣ ይህን ሐሳቡንም በሰላማዊ መንገድ የመግለጽ መብት አለው::

4.6.9 አንድ ሰው የግል ሐሳቡንና እምነቱን በአመጽ፣ በዛቻ ወይም ሌላ ይህን በመሰለ ሕገወጥ መንገድ የሌሎችን መብት በመጋፋት ተፈጻሚ ለማድረግ ሞክሮ ካልሆነ በስተቀር፣ በአገራዊ ጉዳይ ላይ የመሰለውን ሐሳብ በመያዙና ሐሳቡን በመግለጹ ወንጀለኛ አይደለም::
ወ/ሮ ንግስት መኳንንት የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተከሣሾች ከዚህ በላይ ከተገለጸው ንግግር ውጪ ዛቻ ይናገሩ ነበር ወይ ተብለው ከፍርድ ቤቱ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ዛቻ አልነበረም በማለት ገልጸዋል:: ተከሣሾች በመከላከያ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ እንዳስረዳነው እጅግ ሚዛናዊ በሆነ አስተያየት የአገራችን አስጨናቂ የፖለቲካ አጣብቂኝ እንዲፈታ ጥረት ከማድረግ ውጪ በአንዳችም የወንጀል ሐሳብና ተግባር አልተገኘንም:: ተከሣሾች ተሳታፊ የነበርንባቸው የሲቪል ማህበረሰቡ ስብሰባዎችም ፍጹም ሰላማዊ እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የአገራቸው ጉዳይ ያሳሰባቸው ዜጐች በነፃነት ስሜት የተወያዩበት፣ የተከራከሩበት፣ የመከሩበት፣ ዲሞክራሲያዊ መድረኮች ናቸው:: በእነዚህ መድረኮች የመሰላቸውን ሐሳብ የገለጹ ተሳታፊዎች ሁሉ ሐሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለጽ መብታቸውን ከመጠቀም ውጪ አንዳችም ሕገወጥ ተግባር አልተከናወነም፣ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ከዚህ በላይ የተገለጸው አይነት ንግግር ሰምተናል ከሚሉ በስተቀር፣ ዛቻ ወይም ሕገወጥ እንቅስቃሴ እንዳልነበረ አረጋግጠዋል::

4.6.10 ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በተከሣሾች ላይ ከቀረበው ክስና ማስረጃ እንዲሁም ከአጠቃላይ የነገሩ ሁኔታ ለመገንዘብ የሚቻለው ከተከሣሾች በላይ ተከሳሽ ሆነው ለዳኝነት የቀረቡት ጉዳዮች :-

- የአመለካከት እና ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት ፣
- የመደራጀትና የዜጐች በአገራቸው ጉዳይ የመሳተፍ መብት እና

- የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የመሳተፍ መብት ናቸው ::

ሁለታችንም ተከሣሾች በእነዚህ መብቶቻችን በኃላፊነት ስሜት ጭምር ከመጠቀማችንና ጠቃሚ ተግባሮች ከማከናወናችን በስተቀር በአንዳችም የወንጀል ስራ ፈጽሞ ተሳትፎ የለንም ::

## 4.7 ስለ ተከሣሾች ባሕሪ እና አስተዋጽኦ የተሰጠ ማረጋገጫ

4.7.1 ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ተከሣሾች ከተከሰሱበት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ስለነበራቸው ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ ተሳትፎና አስተዋጽኦ እጅግ በርካታ በሆኑ የሰው ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ ያስረዱ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ሁለቱም ተከሣሾች የዘወትር ባሕሪያቸውና ተግባራቸው በዐቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ከተገለጸው ፀረ-ሰላማዊነት፣ አመጸኝነትና ሕገወጥነት ጋር ፈጽሞ የማይገናኝና ይልቁንም እጅግ የተለየ ሰላማዊነትና ሕጋዊነት የሞላበት መሆኑን ለማስረዳት በአቀረቡዋቸው የባህሪ ምስክሮችና ማረጋገጫ ሰነዶች (character testimony) በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል::

4.7.2 ከተከሣሾች የመከላከያ ምስክሮች ውስጥ በተለይ የተከሣሾችን መልካም ባህሪና ሰላማዊ ዜግነት (peacable nature) እንዲሁም ከፍተኛ ጽናት የተሞላው ሰላማዊ አስተዋጽኦዎች እና በሲቪል ማህበረሰቡ ዘንድ የነበራቸውን ሕጋዊና ሰላማዊ ተሳትፎዎች በሚመለከት 10ኛው ምስክር ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ፣ 11ኛው ምስክር ሚ/ር ሪቻርድ ቼምበርስ፣ 22ኛው ምስክር አቶ ወንድወሰን ስንታየሁ፣ 53ኛው ምስክር አቶ አበበ ወርቁ፣ 120ኛ ው ምስክር ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ፣ 123ኛው ምስክር አቶ ፍቅሬ ዘውዴ፣ 125ኛው ምስክር ዶ/ር ቆንጂት ፈቃደ፣ 136ኛው ምስክር አቶ ማሞ ውድነህ፣ 141ኛው ምስክር አቶ ታምራት ከበደ፣ 146ኛው ምስክር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፣እና 155ኛው ምስክር ወ/ት ብዙወርቅ ከተተ በሰጡት የምስክርነት ቃል በከፍተኛ ስሜት አረጋግጠዋል::

4.7.3 ከዚህ በተጨማሪም በማስረጃ ቁጥር 21 ስር የቀረቡት ሰነዶች የተከሳሾችን ሰላማዊነት (Peaceable Nature) ፣ ባሕሪ እና አስተዋጽኦ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች (Character Testimony) ሲሆኑ ፤ በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን ፍሬ ነገሮች አረጋግጠዋል:-

ሀ. በማስረጃ ቁጥር 21.1 እንደተመለከተው ስለ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ምስክርነት የሰጡት ኘሮፌሰር ጋይ ጉድዊን ጊል ናቸው:: ኘሮፌሰር ጉድዊን እንግሊዝ አገር የሚገኘው እጅግ ታዋቂው ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የዓለም ዓቀፍ ሕግ ከፍተኛ ተመራማሪና ምሁር ሲሆኑ፤ እ.ኤ.አ. ከ1997-2002 በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ የአውሮፓ ጥናት ተቋም ዳይሬክተር ፣ ከ1994-2000 በአምስተርዳም ዩኒቨርስቲ የስደተኞች ሕግ ጥናት ሊቀመንበር፣ ከ1989-1994 በካናዳ ካርልተን ዩኒቨርስቲ የሕግ ኘሮፌሰር እንዲሁም ከ1976-1988 በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ውስጥ በሕግ አማካሪነት በዓለም እየተዘዋወሩ ያገለገሉ ና t ው'

ኘሮፌሰሩ Šዚህ በተጨማሪም በዓለም ዓቀፍ ሕግ፣ በሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ እና በስደተኞች ጉዳይ ሕግ ለብዙ መንግስታት፣ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ ለአውሮፓ ሕብረት እና ለአለም ዓቀፍ የፓርላማ ሕብረት ጨምሮ ለልዩ ልዩ ዓለም ዓቀፋዊ ድርጅቶች በአማካሪነት ያገለግላሉ::

ፕሮፌሰሩ ከጻፏቸውና በኦክስፎርድ አሳታሚ ድርጅት አማካኝነት ከታተሙት እጅግ ታዋቂ መጻሕፍቶች ውስጥ ስለ ዓለም ዓቀፍ ሕግ ፣ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ- ዓለም ዓቀፍ ሕግና ልምድ ፣የሰብአዊ መብቶች መሠረታዊ ሰነዶች ፣ የልጅ ወታደሮች ፣ እና የሰዎች ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ በዓለም ዓቀፍ ሕግ የተሰኙት ይገኙበታል::

ኘሮፌሰር ጉድዊን ስለ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ በሰጡት የምስክርነት ቃል፣ ዳንኤል በቀለ ከእንግሊዝ መንግስት የውጭ ጉዳይ ቢሮ በተሰጠው የቼቪኒግ ትምህርት ዕድል በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለማስተርስ ዲግሪ ትምህርትና ጥናታዊ ምርምር በሚያደርግበት ወቅት በእርሳቸው ክትትልና አማካሪነት ስር እንደነበር ገልጸው በተለይ የሚከተለውን ማረጋገጫ ሰጥተዋል:-

- ዳንኤል በቀለ በትምህርቱ እጅግ የላቀ ችሎታና ውጤት በማሳየቱ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ማዕረግ እንደተመረቀና በዚህም ለዶክትሬት ማዕረግ ጥናትና ምርምር እንዲዛወር የተደረገ መሆኑን፣
- በዳንኤል በቀለ መልካም ሥነ ምግባር፣ ሐቀኝነት እና ቁምነገረኛነት ከፍተኛ ስሜት እንዳደረባቸውና፣ እንኳንስ የአመጽ እንቅስቃሴ ሊያነሳሳና ሊያበረታታ ይቅርና እንደዚህ ያለውን ነገር በሐሳብ ደረጃ እንኳን ይቀበላል ብለው ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንደማያምኑ፣ ይልቁንም ዳንኤል በቀለ በሕግ የበላይነት እጅግ የጠነከረና መሰረት የያዘ እምነት ያለው፣ ለሰብዓዊ

መብቶች፣ ለሰው ልጅ ነፃነትና ለሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ሒደት ጥልቅ የሆነ ጽናትና እምነት ያለው፣ በአጭሩ ሙያዊ ብቃቱም ሆነ በሲቪል ማህበረሰብ ወስጥ ሐቀኝነቱ በአንድ ጊዜ ሊታይ የሚችል ሰው ነው በማለት ማረጋገጣቸውን ፣

ለ. በማስረጃ ቁጠር 21.2 እንደተመለከተው ስለ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ምስክርነት የሰጠው ዋና መስሪያ ቤቱ በካናዳ ዋና ከተማ ኦታዋ የሚገኘው ኦክስፋም ካናዳ የተባለው ዓለም ዓቀፍ የልማትና ሰብዓዊ ድርጅት ሲሆን፤ በተለይ የሚከተለውን አረጋግጧል፡-

- ዳንኤል በቀለ በኦክስፋም ካናዳ የአፍሪካን ቀንድ የአቅም ግንባታ ኘ ሮግራም ወስጥ የብሔራዊ አማካሪ ቦርድ አባል በመሆን ኘሮግራሙ ለአፍሪካ ቀንድ ተስማሚ እንዲሆን በከፍተኛ እውቀትና ችሎታ አስተዋጽኦ ማድረጉን ፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ ኘሮጀክቶች በተለይም ስለ ማህበረሰብ የመረጃ ማዕከልና የማህበረሰብ ሬድዮ መጀመርን በሚመለከት ስለአደረገው አስተዋጽኦ፣
- ኦክስፋም ካናዳ በአፍሪካ ቀንድ ሊከተል ስለሚገባው የረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ ፖሊሲ ቀረጻ ውስጥ ስላደረገው እጅግ ጥልቅ አስተሳሰብ የተሞላው አስተዋጽኦ፣
- ከዳንኤል በቀለ ጋር ለረጅም ጊዜ አብሮ በመስራት ለማረጋገጥ እንደቻሉት የሰላም ሰው እንደሆነ ፣ሰዎችንና ማህበሮቻቸውን ወይም ተቋሞቻቸውን የሚያከብር፣ ልዩነቶችን በውይይትና በድርድር ለመፍታት የፀና አቋም ያለው መሆኑን እንደሚመሰክሩ፣ ሁልጊዜም ቢሆን ለሐቀኛ ውይይት ፅናት ያለው፣ አንዳችም ጊዜ የተደበቀ አጀንዳ ያልነበረውና የተደበቀ አጀንዳ የማያራምድ፣ አመጽ፣ አፍራሽ የሆነ ሥራ እና ፍጥጫ ያለበትን ሐሳብ፣ ባህሪ፣ አቋም ወይም ተግባር ፈጽሞ የማይደግፍ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ፣
- ከዳንኤል በቀለ ጋር በነበራቸው ግንኙነቶች ሁሉ በመርህ የሚመራ ሰላማዊ ሰው እና በሰዎች መካከል መተማመን እንዲጐለብት በጽናት የሚጥርና የሚሰራ መሆኑን፣ ስለ አገሩ ዜጐች ጥልቅ የሆነ ስሜትና ፍቅር ያለው፣ ለኦክስፋም ካናዳ ሠራተኞች ጭምር እስከ አሁን ድረስ እንደ አርአያ የሚታይ መሆኑን አረጋግጠዋል።

ሐ. በማስረጃ ቁጥር 21.3 እንደተመለከተው ስለ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ምስክርነት የሰጡት ዋና መስሪያ ቤቱ አሜሪካን አገር ዋሽንግተን ከተማ የሚገኘው ፓክት የተባለው ዓለም ዓቀፍ የልማት ድርጅት የኢትዮጵያ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት ሚ/ስ ሌዝሊ ሚሽል ሲሆኑ፣ በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን አረጋግጠዋል፡-

- ዳንኤል በቀለን ለአስር ዓመት ያህል እንደሚያውቁትና በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ ስለአደረገው በርካታ አስተዋጽኦ፣
- ዳንኤል በቀለ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ሥነ ምግባር የሚመራና የሚሰራ፣ ከፍተኛ የሐዘኔታ ስሜት ያለው ለኢትዮጵያና ዜጎችዋ በከፍተኛ ጽናትና መስዋእትነት የሚሰራ፣ ወገንተኛ ያልሆነ፣ ሁሉንም ወገኖች ለማስማማት የሚችል የመፍትሔ ሐሳብ ለማግኘ ት የሚጥር፣ ለሕጋዊ ሥርዓትና አሰራር ታማኝ የሆነ፣ እውነትና ፍትሕን አጥብቆ የሚሻ ፣ሰላማዊ የሆነና ፍጥጫን የማይወድ መሆኑን ፣ችግሮችና ልዩነቶች የሚፈቱት በመግባባትና በመከባበር ነው ብሎ የሚያምን ሰው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

መ. በማስረጃ ቁጥር 21.4 እንደተመለከተው ሰለ 95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ምስክርነት የሰጡት በግንቦት 97 የኢትዮጵያ ምርጫ ሒደት ጉልሕ ተሳትፎ የነበረው Electoral Reform International Service (ERIS) የተባለው ዓለም ዓቀፍ ተቋም ሥራ ኃላፊ የነበሩት እንዲሁም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካሪ የነበሩት በተከሣሾች 11ኛ መከላከያ ምስክርነትም ቀርበው የነበሩት ሚ/ር ሪቻርድ ቻምበርስ ናቸው፡፡ ሚ/ር ሪቻርድ ቻምበርስ በኢንግላንድ እና ዌልስ በሕግ ባለሙያነት የሰሩ& እ.ኤ.አ. ከ1995-1999 በግጭት ማስወገድ ሥራ ላይ የተሰማሩ& ከ1995 ጀምሮ ከሃያ በላይ በሚሆኑ አገሮች ውስጥ በምርጫ ጉዳይ የሰሩ፣ ለአውሮፓ ሕብረት፣ ለአውሮፓ ደህንነትና ትብብር ድርጅት እንዲሁም ለበርካታ መንግስታት በምርጫ ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ አማካሪነት የሰሩ ሲሆን ኢትዮጵያ ውሰጥ በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት ይሰሩ በነበረበት ጊዜም በ95ኛው ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ የሚመራው ድርጅት ሲያስተባብር የነበረውን «የአገር ውስጥ ሲቪል ማህበረሰብ ምርጫ ታዛቢዎች ቅንጅት» ስራንም በቅርብ ሲከታተሉ የነበሩ መሆኑን ገልጸው በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን አረጋግጠዋል፡-

- ከነፃነት ደምሴ ጋር በነበራቸው ቀጥተኛ ግንኙነት ለመገንዘብ እንደቻሉት የሲቪል ማህበረሰብ ሥራዎች በገለልተኝነት እንዲከናወን ስለነበረው የፀና የመርሕ አቋም፣ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ስለነበረው ድጋፍ እና ለሕጋዊና ሕገመንግሥታዊ አሰራር ለሕግ የበላይነት ከበሬታና እውቅና የሚሰጥ መሆኑን እንዳረጋገጡ፣
- ከምርጫው ሒደት ጋር በተያያዘ ከነፃነት ደምሴ ጋር በነበራቸው ግንኙነትና ውይይት ሙያዊ ብቃቱን ገለልተኝነቱንና በሐቀኝነት የሚሰራ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተው ማረጋገጣቸውን በተለይም በምርጫው ሒደት ወቅት በገለልተኝነት መርህ ይሰራ እንደነበር በጣም በግልጽ ለማየት እንደቻሉ እንደሚያረጋግጡ፣
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአገር ውስጥ ታዛቢዎች ላይ ገደብ በጣለበት ወቅት ነፃነት ደምሴና እርሱ ይመራው የነበረው ድርጅት ጉዳዩን ወደ ጋለ የፖለቲካ ጥያቄ  ከመለወጥ ይልቅ መብታቸውን በሕግ ለማስከበር ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ለሕጋዊ አሰራር ያሳዩት ፅናት በከፍተኛ ደረጃ አድናቆት እንዳሳደረባቸው በምርጫው ወቅት ሁሉ ነፃነት ደምሴ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠራተኞች ጋር በነበረው መልካም የሥራ ግንኙነትና የመከባበር መንፈስ ከፍተኛ አድናቆት እንዳሳደረባቸው፣
- ከምርጫው በኋላም ከነፃነት ደምሴ ጋር በቅርብ ይሰሩ እንደነበር፣ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረቡ እጅግ በርካታ የምርጫ ቅሬታዎች ሊጣሩና ሊወሰኑ ስለሚገባበት ሕጋዊ አሰራር አንድ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት ከነፃነት ደምሴ ጋር ምክክር በማድረግ ጠቃሚ ሐሳቦች መውሰዳቸውንና በዚሁ መሠረትም የምርጫ ቅሬታ አጣሪ አካሎች መቋቋማቸውን፤ ነፃነት ደምሴ ይህን ሒደት መደገፉና ፤ በምርጫ ቦርድ በተደረጉ ስብሰባዎች የእነ ነፃነት ደምሴ በፍርድ ቤት የመገልገል አካሄድ አለመግባባቶችን በሕጋዊ መንገድ ለመፍታት በጥሩ ምሳሌነት መወሰዱ፤ ነፃነት ደምሴ ሁሉም ወገኖች በሕጋዊው የቅሬታ ማጣራት ሥርዓት እንዲሳተፉ እንዳበረታታ አረጋግጠዋል፡፡
- የፖለቲካ ቀውስ እየተባባሰ በሄደበት ወቅት ነፃነት ደምሴ በሁኔታው እጅግ ያዝንና ይጨነቅ እንደነበር፣ ሁሉም ወገኖች የፖለቲካውን ውጥረት በሰላማዊ መንገድ ሊፈቱ ይገባል ብሎ ያምን እንደነበር፣ ለዚህ ዓይነት ሰላማዊ ጥረትም ተሳታፊ እንደነበር ከዚህ ሁሉ

በመነሳት ነፃነት ደምሴ ለዲሞክራሲ፣ ለሰብዓዊ መብቶች እና ለሕግ የበላይነት የፀና እምነት ያለው ሁልግዜም በሐቀኝነት በርትዓዊ መንገድ ይሰራ የነበረ እንጂ ሌላ ዓላማ ያልነበረው ሰላማዊ ዜጋ መሆኑን እንዳረጋገጡ ገልጸዋል፡፡

ሠ. በማስረጃ ቁጥር 21.5 እንደተመለከተው ስለ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ ምስክርነት የሰጡት አክሽን ኤድ የተባለው ዓለም ዓቀፍ የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት ሚ/ር ራሚሽ ሲንግ ናቸው፡፡ ሚ/ር ራሚሽ በትምህርታቸው ከኔፓል ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ማዕረግ የአገሪቱ ንጉስ የወርቅ ተሸላሚ ሆነው የተመረቁ፣ እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ኤደንብራ ዩኒቨርስቲ በማስተርስ ዲግሪ የተመረቁ፣ በኢትዮጵያ የአክሽን ኤድ ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣ በእስያ አህጉር የአክሽን ኤድ ዳይሬክተር፣ ከዚያም በአክሽን ኤድ ዓለም ዓቀፍ በዋናው ጽ/ቤት የኦኘሬሽን ዳይሬክተር የነበሩና አሁን በመጨረሻም በ48 አገሮች ውስጥ የሚካሄደው እጅግ ግዙፍ የሆነው የአክሽን ኤድ ዓለም ዓቀፍ የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆን በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን አረጋግጠዋል፡-

- ዳንኤል በቀለ ሐቀኛ እና ቁምነገረኛ ደስ የሚያሰኝና ሰው አክባሪ የሆነ የሰዎችን ሐሳብ የሚያደምጥ ከፍተኛ እውቀት ያለው ለዲሞክራሲና ማህበራዊ ፍትሕ እሴቶች የፀና እምነት ያለው ሰው መሆኑን እንደሚያረጋግጡ፣
- ዳንኤል በቀለ የሕግ ባለሙያ በመሆኑ ጭምር አጠቃላይ የድርጅቱ ስራ በሕጋዊ አሰራር መካሄዱን ጭምር የሚመራና የሚቆጣጠር መሆኑን በማረጋገጥ ያሰራ እንደነበር፣
- ዳንኤል በቀለ እጅግ በርካታ ጠቃሚ ሥራዎችን በፌደራልም ሆነ በክልል ከመንግሥት አካሎች ጋር በመልካም ግንኙነት የሚያካሂድ በዚህም የአክሽን ኤድ ስራ በኢትዮጵያ ውሰጥ ከፍተኛ ምስጋና ያተረፈ መሆኑን፣
- አክሽን ኤድ በሚሰራባቸው አገሮች ሁሉ በሕግ በተፈቀደለት መንገድ ብቻ የሚሰራ መሆኑንና የኢትዮጵያ ኘሮግራም ስራም ከዚህ የተለየ አለመሆኑን፣
- ዳንኤል በቀለ በጠቅላላው በአክሽን ኤድ ወስጥ እጅግ የተመሰገነ፣ ተወዳጅ የሆነ፣ የተከበረና መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ የሚደነቅ ሠራተኛ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ፣ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ለሚሰሩ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ፣ ያከናወናቸው ተግባሮችም በሙሉ በአክሽን ኤድ ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት የተከናወኑ ሥራዎች መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ ገልጸዋል፡፡

ረ. በማስረጃ ቁጥር 21.6 እንደተመለከተው ለ94ኛ ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ እና ለ95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ምስክርነት የሰጡት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚሊኒየም ዘመቻ ዳይሬክተር የሆኑት ሚ/ር ሳሊል ሸቲ ሲሆኑ በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን አረጋግጠዋል፡-

- ነፃነት ደምሴና ዳንኤል በቀለን በተባበሩት መንግሥታት እና በሲቪል ማህበረሰቡ አማካኝነት በሚካሄደው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ድህነት ዘመቻ ውስጥ በአላቸው ተሳትፎና አስተዋጽኦ የተነሳ ከሶስት ዓመት በላይ እንደሚያውቋቸው፤ ሁለቱም በዓለም ዓቀፍ የልማት ግቦች በጽናት የሚሰሩ መሆኑን፤ አንዳቸውም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በአመጽ ስራ ተሳትፈዋል ብለው ፈጽሞ ሊያምኑ እንደማይችሉ ይልቁንም ሁለቱም ሰዎች ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ ያላቸው፣ ከፍተኛ የሞራልና የስነ ምግባር ደረጃ የሚጠብቁ፣ ለሰው ልጆች ጥልቅ የሆነ ክብር ያላቸው፣ በሰብዓዊ መብቶችና በሕግ የበላይነት የሚያምኑ መሆኑን እንደሚያረጋግጡና ሁለቱንም በግል ቀረቤታ ጭምር ስለሚያውቋቸው ረጋ ያሉ እና አስተዋይ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ፣
- ከነፃነት ደምሴና ከዳንኤል በቀለ ጋር በቀጥታ ካላቸው ግንኙነት በመነሳትም ሆነ ሌሎች ሰዎች ስለእነሱ እንደሚናገሩት በሚያውቁት መጠን ሁለቱም ሰዎች ለአገራቸውና በተለይም ለድሀው የሕብረተሰብ ክፍል ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ እራሳቸውን መስዋእት እስከ ማድረግ ድረስ የሚሰሩ እጅግ የተከበሩ ዜጎች መሆናቸውን ሳረጋግጥ ያለአንዳች ጥርጣሬ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

ሰ. በማስረጃ ቁጥር 21.7 እንደተመለከተው ለ94ኛ ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ እና ለ95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ምስክርነት የሰጡት ሲቪከስ (CIVICUS) የተባለው ዓለም ዓቀፍ የሲቪል ድርጅቶች ትብብር ዋና ፀሐፊ የሆኑት ዶ/ር ኩሚ ናይዶ ናቸው፡፡ ዶ/ር ኩሚ እንግሊዝ አገር ከሚገኘው የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስ ጥናት በዶክትሬት የተመረቁ፣ ቀደም ሲል የደቡብ አፍሪካ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር የነበሩ እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1994 በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሲካሄድ የምርጫ ኮሚሽኑ ዳይሬክተር የነበሩ፣

በደቡብ አፍሪካ የፀረ-አፓርታይድ ትግል ዋነኛ ተዋናዮች ውስጥ አንዱ የነበሩ፣ በዩኒቨርስቲ መምህርነትና በተመራማሪነት ያገለገሉ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ለሲቪል ማህበረሰቡ የግንኙነት መድረክ የዓለም አጅግ ታዋቂ ሰዎች ፓናል ውስጥ በአባልነት የተሰየሙ፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶችና የክሊንተን ፋውንዴሽን አማካሪ ቦርድ አባል ናቸው:: ዶ/ር ኩሚ ስለ ዳንኤልና ነፃነት በሰጡት ምስክርነት በተለይ የሚከተለውን አረጋግጠዋል፡-

- ዳንኤል በቀለና ነፃነት ደምሴን በተለይ በዓለም ዓቀፍ የፀረ-ድህነት ዘመቻ አብረው ሲሰሩ በቅርብና በቀጥታ እንደሚያውቋቸው፣ ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች የሥራ ጓደኞቻቸው አማካኝነትም ስለ እነርሱ ያውቁ እንደነበር፤ እራሳቸው በቀጥታ በሚያውቁት መሠረት ሁለቱም ለሰላማዊ የሲቪል ማህበረሰብ እንቅስቃሴ በጽናት የቆሙ መሆኑን እንደሚያምኑ፣ እንደሚያረጋግጡና መታሰራቸውን ሲሰሙ በእጅጉ እንደደነገጡ፣
- እነዚህ ሁለት ሰዎች ማለትም ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ በአገራቸው ብቻ ሳይሆን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በፀረ-ድህነት ዘመቻ በመልካም አስተዳደርና የፍትሕ እንቅስቃሴ ውስጥ እጅግ የተመሰገኑ፣ በአድናቆትና በክበሬታ የሚታዩ ታዋቂ ሰዎች መሆናቸውን
- የእነዚህን ሁለት ታዋቂ ዜጐች መታሰር እንደሰሙ ከደቡብ አፍሪካው የተከበሩ ብፁዕ ጳጳስና የተባበሩት መንግስታት የሚሊኒየም ዘመቻ ዳይሬክተር ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ማነጋገራቸውን፣ ዳንኤልና ነፃነትንም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈቃድ እስር ቤት ሄደው መጐብኘታቸውን፣
- ዳንኤል በቀለም ሆነ ነፃነት ደምሴ ሰላማዊና ተገቢ ያልሆነ የሲቪል ማህበረሰብ ስራ ላይ ይሰማራሉ ብለው ፈጽሞ እንደማያምኑና ይህንንም በእርግጠኝነት እንደሚናገሩ፤ ሁለቱም እጅግ ጠንካራ ሥነ ምግባር ያላቸው ሰዎች ስለሆኑ በሚያምኑበት ነገር በሙሉ ልባቸው ጸንተው የሚቆሙ ሰዎች መሆናቸውን እንደሚያውቁ፤ ፍትሕ የሚገኘው በሰላማዊ ትግል መሆኑን አበክረው የሚያምኑ፣ የአገራቸውን ሰላም አጥብቀው የሚሹ፣ ስለአገራቸው የሚያስቡና የሚጨነቁ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ፣
- በአለፉት ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ የሲቪከስ ዋና ፀሐፊ ሆነው በአገለገሉበት ዘመን ብዙ ለዲሞክራሲና ለልማት ስራ ፅናት ያላቸው ሰዎችን እንደሚያውቁና ዳንኤልና ነፃነት ከእነዚህ ጥቂትና ምርጥ ሰዎች ውስጥ

መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ፣ በተፋጠነ ሁኔታ ከእስር ተለቀው ለአገራቸው ጠቃሚ ስራ መስራታቸውን ይቀጥላሉ ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገልጸው፤ ጉዳያቸውን እየተመለከተ ያለው የተከበረው ፍርድ ቤት ስለእነዚህ ሁለት ታላቅ የሥራ ጓደ…ቻቸው መልካም ሥነ ምግባርና ክብር የሰጡትን ምስክርነት እንዲቀበላቸው ጠይቀዋል።

ሸ. በማስረጃ ቁጥር 21.8 እንደተመለከተው ስለ 95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ምስክ ርነት የሰጡት የግንቦት ምርጫ 97 ሒደት በዓለም ዓቀፍ ታዛቢነት የተሳተፈው የካርተር ማዕከል የኢትዮጵያ ቢሮ ምክትል ኃላፊ የነበሩት ሚስ ሶፊ ካን ናቸው። ሚስ ሶፊ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከካናዳ ብሪትሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ፣ የማስተርስ ዲግሪያቸውን አሜሪካን አገር ከሚገኘው ዓለም ዓቀፍ የስልጠና ኢኒስቲትዩት ያገኙ ሲሆን ፤ በተባበሩት መንግሥታት፣ በካርተር ማዕከል፣ በካናዳ ዓለም ዓቀፍ የልማት ባለሥልጣን (CRDA) እና ሌሎችም ድርጅቶች ውሰጥ በልማት ሥራ እና በምርጫ ጉዳዮች ላይ ሰርተዋል። በተለይም በኢንዶኔዥያ፣ በኢስት ቲሞር፣ በፍልስጤም ምዕራብ ዳርቻ እና በኰንጎ እንዲሁም በኢትዮጵያ በግንቦት 97 ምርጫ ሒደት የሰሩ ሲሆን፤ በተለይ ከዚህ በታች የተመለከተውን አረጋግጠዋል፡-

- በኢትዮጵያ ይሰሩ በነበረበት ወቅት ከነፃነት ደምሴ ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት ይነጋገሩ የነበረ መሆኑንና እርሱም ሆነ ይመራው የነበረው ድርጅት በሙያ ብቃትና በገለልተኝነታቸው ይታወቁ የነበረ ስለሆነ የካርተር ማዕከል ለምክክር ከሚያነጋግራቸው ድርጅቶች ውስጥ እንደነበር፣
- ነፃነት ደምሴ በግልም ሆነ በይፋ በሚሰጠው አስተያየት ሚዛናዊ የሆነ፣ የጥላቻና የፀብ ንግግር የማያደርግ፣ የተሳሳተ መረጃ የማይሰጥ ሰው ስለሆነ አስተያየቱን ሁሉ ያከብሩ እንደነበረና ከዚህም የተነሳ የካርተር ማዕከል ኘሬዚደንት ጂሚ ካርተር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ካነጋገሯቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳይ የነበረው አስተያየት ሙያዊና በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ለነፃነት ደምሴ አክብሮት እንዳላቸው ገልጸዋል።

## 4.8 ስለተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃዎች ብቃት

4.8.1 ተከሣሾች የቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል ያቀረቡዋቸው የመከላከያ ምስክሮችና ሰነዶች በአጠቃላይ ከፍተኛ ብቃት እና ክብደት ያላቸው፡ ተዓማኒነታቸው የማያጠራጥር ተጨባጭ የሆኑ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

የመከላከያ ምስክሮቹ በትምህርት ደረጃቸው ከመጀመሪያ ዲግሪ አንስቶ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ እና የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ድረስ የደረሱ፣ በሥራ ልምዶቻቸው በልዩ ልዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች፣ በዩኒቨርስቲዎች፣ በምርምር ተቋሞች፣ በፍትሕ አስተዳደር አካላት እጅግ በከፍተኛ ኃላፊነት ጭምር ያገለገሉ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንስቶ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ በዳኝነት ያገለገሉ፣ በዐቃቤ ሕግነት ያገለገሉ፣ በዩኒቨርስቲ መምህርነት ያገለገሉ፣ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ታላቅ ከበሬታና እውቅና የተሰጣቸው የታሪክ፣ የሕግ፣ የሳይንስ፣ የፖለቲካ፣ የጋዜጠኝነትና የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሮች፣ እጅግ ጥልቅ የሆነ ከበሬታ የሚሰጣቸው ታላላቅ ኢትዮጵያውያንና፣ እንዲሁም እጅግ ሰፊና ጥልቅ ልምድ ያላቸው ዓለም ዓቀፋዊ እውቅና ያላቸውን ምሁሮችና የዓለም ዓቀፋዊ ድርጅቶች መሪዎች ይገኙበታል፡፡

4.8.2 በአንጻሩ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በትምህርት ደረጃቸው ከማንበብና መጻፍ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ድረስ ብቻ የተማሩ፣ በሥራ ረገድ አንደኛው ሥራ አጥ መሆኑን የገለጸ፣ ሌላኛው ደላላ መሆኑን የገለጸ፣ ሁለቱ ደግሞ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባሎች መሆናቸውን የገለጹ ናቸው፡፡

4.8.3 ተከሣሾች በተከሰሱበት ጉዳይ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ስለተጠቀሱት የኢትዮጵያ ሆቴል፣ የግሎባል ሆቴል፣ የCRDA እና ቀይ መስቀል አዳራሽ ስብሰባዎች በተመለከተ በየስብሰባዎቹ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች ስም ዝርዝር ጭምር በማስረጃነት የቀረበ ስለሆነ በተመሳሳይ የፍሬ ነገር ጭብጥ የፍርድ ቤቱን የስራ ጊዜ ማባከን አስፈላጊ ባለመሆኑ እንጂ ቢያስፈልግ በየስብሰባዎቹ የነበሩ በድምሩ ከ300 /ሶስት መቶ/ በላይ ምስክሮች ሊቀርቡና እስከ አሁን በቀረቡት ምስክሮች በበቂ ሁኔታ የተረጋገጠውን ግዙፍ ሐቅ ሊያረጋግጡ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ስለ ተከሣሾች ሕጋዊና ሰላማዊ ስራዎች ስለ ሰላማዊ ዜግነታቸውና አስተዋጽኦዋቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ምስክሮች ቀርበው ሊያረጋግጡ ይችላሉ፡፡

**4.8.4** በሰነድ ማስረጃ ረገድም ተከሣሾች ተሳታፊ ስለነበሩባቸው የሲቪል ማህበረሰቡ የስራ እንቅስቃሴዎች ጠቅላላ ሒደቱን የሚያመለክቱ የተሟሉ ተጨባጭ የሰነድ ማስረጃዎችን፣ ተከሣሾች ከልዩ ልዩ ጋዜጦች ጋር የአደረጉትን ቃለ ምልልስ የጋዜጣዎቹን ቅጂዎች፣ ተከሣሾች ተሳታፊ ስለነበሩበት የሲቪል ማህበረሰቡ የስራ እንቅስቃሴዎች የተመለከቱ ልዩ ልዩ ተጨባጭ የሰነድ ማስረጃዎችን፣ የተከሣሾችን አስተዋጽኦ በተመለከተ እንደ ናሙና ማስረጃነት ሊታዩ የሚችሉ ተጨባጭ የሰነድ ማስረጃዎችንና የተከሣሾችን ባህሪ በተመለከተ የተሰጡ ማረጋገጫዎች ይገኙበታል።

**4.8.5** ተከሣሾች በአቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች እጅግ የሚበዙ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎችም ለማቅረብ እንችል ነበር። ነገር ግን ከዚህ በፊት ለፍርድ ቤቱ እንዳሳወቅነው በኰምፒውተሮቻችን ውስጥ የሚገኙ ሰነዶችን ለማሰባሰብ በተደጋጋሚ በተፈጠረብን መሰናክል የተነሳ በኰምፒውተር ውስጥ የሚገኙ የመከላከያ ማስረጃዎቻችንን ለማሰባሰብ እንዳንችል በመደረጋችን ለመተው የተገደድን መሆኑን ገልጸናል።

ይሁንና ተከሣሾች እጅግ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ቢሆንም ለማሰባሰብ የቻልናቸው የመከላከያ ማስረጃዎች እጅግ ከበቂ በላይ በመሆናቸውና የተፋጠነ ፍትሕ ለማግኘት እንድንችል በአቀረብናቸው ማስረጃዎች ውሳኔ እንዲሰጠን የጠየቅን ቢሆንም ተከሣሾች የቀረበብንን ክስ በመከላከል ረገድ የገጠመንን መሰናክሎች ግን ፍርድ ቤቱ ግምት ይወስድታል ብለን እናምናለን።

**4.8.6.** ተከሣሾች ያቀረብነውን የባሕሪ ወይም የጠባይ ማስረጃዎች በሚመለከት ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ በአቀረበው አስተያየት እንደዚህ ያለው ማስረጃ ሊቀርብ የማይችልና ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የገለጸው ፈጽሞ የተሳሳተና ከማስረጃ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች የራቀ አስተያየት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ገና በአዋጅ የጸደቀ የማስረጃ ሕግ የሌለ ቢሆንም እንኳን በማስረጃ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት፣ በረቂቅ የማስረጃ ሕጉ በተመለከተው መሠረት፣ በዳበረው የዳኝነት ሥራ ልምድ መሠረት እና በመሠረታዊ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር መርሆች መሠረት በወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሣሹ ጥሩ ጠባይ ያለው መሆኑ ሁልግዜም ቢሆን አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው። (በረቂቅ የማስረጃ ሕጉ አንቀጽ 47 ላይ በግልጽ ተመልክቷል።)

**4.8.7.** በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ማናቸውም ሰው ስለ ጥሩ ጠባይ ማስረጃ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑ በሁሉም አገሮች የወንጀልና የማስረጃ ሕግ ውስጥ የታወቀና የተለመደ አሰራር ሲሆን በተለይም ተከሣሹ በተከሰሰበት ጉደይ አግባብነት ያለውን መልካም ስሙን ወይም ዝናውን እና ትግብርቱን ሊያስረዳ ይችላል፡፡

በዚሁ መሠረት ተከሣሾች በተከሰሱበት ጉዳይ በቀጥታ አግባብነት ያለውን ማለትም ሰላማዊ ሰውነታቸውን (peaceable nature)፣ ሕግና ሥርዓት አክባሪነታቸውን፣ እና ጥሩ ጠባያቸውን በተመለከተ በአገር ውስጥና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ጭምር ያተረፉትን መልካም ስም እጅግ ታላቅ በሆኑ ሰዎች ምስክርነት አረጋግጠዋል፡፡ በአገር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በፍ/ቤቱ ፊት እየቀረቡ መስክረዋል፤ በውጭ አገር የሚገኙም ሰዎች የሰነድ ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡

**4.8.8.** ዐቃቤ ሕግ የህን ግዙፍ ሐቅ ውሸት ነው የሚል ቢሆን ኖሮ ብቻ ስለ ተከሣሾች መጥፎ ባሕሪ ማስረጃም ሊያቀርብ ይችል ነበር፡፡ (ረቂቅ የማስረጃ ሕግ አንቀጽ 47(2) ይመለከቷል፡፡) ዐቃቤ ሕግ ይህን ሊናገርም ሆነ ሊያደርግ የሚችለው ባለመሆኑ ከቶውንም አልሞከረውም፡፡ ተከሣሾች ያረጋገጥነውን ኩነት ሊያስተባብለው ባለመቻሉም የተከሣሾች ማስረጃ ተቀባይነት የለውም የሚል ውሃ የማይቋጥር ክርክር መርጧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች የባህሪ ምስክሮች ላይ አንዳችም እንኳን መስቀለኛ ጥያቄ ያላቀረበ ሲሆን አሁንም በሰጠው አስተያየት ስለተከሣሾች መልካም ባሕሪና ትግብርት የተረጋገጠው ኩነት ትክክል አይደለም በሚል ሳይሆን ለክርክር ያህል የባህሪ ምስክርነት ሊሰጥ አይችልም (inadmissible) የሚል ነው፡፡ ይህ በመሰረቱ ትክክል ያልሆነ ከመሆኑም በላይ ዐቃቤ ሕግ ስለ ማስረጃው ተቀባይነት (admissibility) ተቃውሞ ቢኖረው ምስክሮች ሲቀርቡ ተቃውሞ ሳያቀርብ ቆይቶ አሁን ሊቀረብ የሚችልም አይደለም፡፡

**4.8.9.** የተከሣሾች ልዩ ልዩ የሰነድ መከላከያ ማስረጃዎችንና በተለይም ተከ ሣሾች በሲቪል ማህበረሰብ አባልነታቸው ያከናወኑትን ስራዎች የሚመለከቱ ሰነዶችንና ከልዩ ልዩ ጋዜጣዎች ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ በሚመለከት ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ በሰጠው አስተያየት ትልቅ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ከፍተኛ ኃላፊነቱ ፍትሕን ማስጠበቅ እንደመሆኑ መጠን በተከሣሽ የሚቀርብለትን የመከላከያ ማስረጃዎች ሲመረምር ልክ እንደ ዳኛ ተመስሎ፣ ትህትና ተላብሶ ከጨዋ ሰው እይታ አንጻር በሐቀኝነት ሊመዝንና ተገቢውን አስተያየት ሊሰጥ ይገባል እንጂ ቃል እጠሰነጠቁ፣ እየጠመዘዙ፣ ቆርጠው

እየቀጠሉ፣ ትርጉም እጠፈጠሩ ተከሳሽን በግድ ላስወንጅለ ብሎ መሟገት ከኃላፊነትም ከሙያ ሥነ ምግባርም ውጪ ነው፡፡

4.8.10. የማስረጃ አስፈላጊነት በመሠረቱ አንድን ኩነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ማስረጃን የመመዘን ነገር እንኳንስ የሕግ ክህሎት ተጨምሮበት ይቅርና ማንም አዕምሮ ግዕዝ ያለው ሰው በጨዋ ሰው ዕይታ ተመልክቶ ሊፈርደው የሚችል ነው፡፡ ተከሣሾች በአቀረብነው የመከላከያ ክርክራችንና ማስረጃዎቻችን በሙሉ አንዳች እንኳን ሐሰት ቢገኝበት ፍረዱብን!

4.8.11. በአንጻሩ ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ከአቀረበው ማስረጃዎች ውስጥ በተለይ አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዩም የሰጡት ምስክርነት፣ መሠረት ወርቁ እና ንግስት መኳንንት የሰጡት ምስክርነት እንዲሁም ለእነ ፍሬዘር ነጋሽ ተጻፈ የተባለው ደብዳቤ አጠቃላይ ሁኔታ ማን በእውነት ማን በሐሰት እንደቆመ ፍንትው አድርጐ ያሳያል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

5.1 በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም ሰው በወንጀል ረገድ ጥፋተኛ የሚባለው ጥፋት የተባለውን ድርጊት የፈጸመ ስለመሆኑ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ (beyond a reasonable doubt) ሲረጋገጥበት መሆኑ ይታወቃል፡፡
በዚህ መሠረት የቀረበበትን የወንጀል ክስ እንዲከላከል ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሰጠበት ተከሳሽ፤ ክሱን በመከላከል ረገድ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ማሳየት ብቻ (to cast a shadow of doubt) በቂ ይሆናል፡፡

5.2 በዚህ እኛ ሁለታችን የሲቪል ማህበረሰቡ አባል የሆንነው ተከሣሾች በተከሰስንበት ጉዳይ የአቀረብናቸው የመከላከያ ምስክሮቻችንና የሰነድ ማስረጃዎቻችን፤ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች ላይ ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ብቻ ሳይሆኑ ከዚህ መስፈርት እጅግ ከፍተኛ ርቀት ተጉዘው ለክሱ ምክንያት በሆኑት ጉዳዮች ሁሉ የሁለታችንን ተከሣሾች ሕጋዊና ሰላማዊ ተሳትፎ እና አስተዋጽኦዎች በተጨባጭ ሁኔታ አረጋግጠዋል፡፡
በሌላ አነጋገር ዐቃቤ ሕግ ተከሣሾች ጥፋተኞች መሆናችንን ከጥርጣሬ ውጪ ሊያስረዳ ካለመቻሉም በላይ፤ ይልቁን እኛው ተከሣሾቹ ጥፋተኞች አለመሆናችንን ከጥርጣሬ ውጪ አስረድተናል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች በተነሱት

ተለይተው በተጠቀሱት ስብሰባዎች እና ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን ፤ ከእነዚህ ስብሰባዎችና ሁኔታዎች በተጨማሪ ስለ ተከሣሾች ተግባርና ምግባር በተጨባጭ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው፤ የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ተስተባብቧል፡፡

5.3 ሁለታችንም ተከሣሾች በቅንነት፣ በሐገር ፍቅር፣ በዲሞክራሲ፣ በሰብዓዊ መብቶችና ማህበራዊ ፍትሕ እምነት ፤ እንዲሁም በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ሕጋዊ፣ ሰላማዊና እጅግ ጠቃሚ ስራዎች ላይ ስንሳተፍ የነበርን ዜጎች እንጂ፤ እንኳንስ ወንጀል ልንፈጽምና የወንጀል ሃሳብም ያለን ሰዎች አይደለንም፡፡

5.4 ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ተከሣሾች በዐቃቤ ሕግ የቀረበውን ክስና ማስረጃዎች እጅግ በተገቢው መንገድ አስረድተናል፡፡ ይኸውም፡-

ሀ. መንግስትን የመገልበጥ የአድማ ወንጀል ሀሳብ የራሳቸው በማድረግ በወንጀል ስራ ተሳታፊ ሆነዋል ስለተባለው፤ ተከሣሾች በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አባልነታችን ሙሉ በመሉ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆኑ ጠቃሚ ስራዎች በመሳተፍ፣ በገለልተኝነት እና በኃላፊነት ስሜት ፖለቲካዊ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት በማድረግ፣ ለአገራችን ሰላም፣ ዲሞክራሲና ሁሉን አቀፍ እድገት የበኩላችንን ጥረት ያደረግን መሆኑን በማስረዳት፣

ለ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ከመሠረታዊ ዓላማቸው ውጪ በማንቀሳቀስ ስለተባለው፤ ተከሣሾች ተሳታፊ የነበርንባቸው የሲቪል ማህበረሰቡ እንቅስቃሴዎች በመሉ በሕግና በፍርድ ቤት ውሳኔ ጭምር የተፈቀዱ፣ በእንቅስቃሴዎቹ ተሳታፊ የነበሩ ሲቪል ማህበራትም ይህንኑ ያረጋገጡ መሆኑን፣ የሲቪል ማህበሩ እንቅስቃሴዎች በፍጹም ግልጽነት የተከናወነ ሕጋዊና ሰላማዊ እንዲሁም እጅግ የተመሰገነ ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንደነበረ በማስረዳት፣

ሐ. ተከሣሾች ሕገወጥ ቅስቀሳ እና ንግግር አድረገዋል ስተባለው፤ ዐቃቤ ሕግ ምስክር ያቀረበባቸውን በአራት ቦታዎች (ግሎባል ሆቴል፣ ኢትዮጵያ ሆቴል፣ ቀይ መስቀል እና CRDA አዳራሽ) የተደረጉት ስብሰባዎች ላይ ተሳታፊ የነበሩ የተከሣሾች መከላከያ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል አንዳችም እንኳን ሕገወጥ ቅስቀሳና ንግግር እንዳልነበር፣ በዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የተባለው ነገር ፈጽሞ ትክክል እንዳልሆነ በማሳየት፣ ይልቁንም በእነዚህ ተለያይተው

በተጠቀሱ አራት ስብሰባዎች ብቻ ሳይሆን ከእነዚሁ ስራዎች ጋር በተገናኙ ሌሎች በርካታ ስብሰባዎችም ጭምር ተከሣሾች ሙሉ በሙሉ በሕጋዊና ሰላማዊ ተግባር ከመሳተፍ ውጪ አንዳችም ጊዜ ሕገወጥ ቅስቀሳ፣ ንግግር ወይም መግለጫ አድርገን እንደማናውቅ በየስብሰባዎቹ እና በእንቅስቃሴዎቹ ተሳታፊ በነበሩ ሰዎችና ጉዳዩን በሚመለከቱ የሰነድ ማስረጃዎች ጭምር በማስረዳት፣

መ. ወጣቶች በአመጽ ተግባር እንዲሳተፉ ተከሣሾች አነሳስተዋል ድጋፍ ሰጥተዋል ስለተባለው፤ ተከሣሾች በተለይ በምርጫው ዘመን በስራ ግንኙነት የነበረን የወጣቶች ማህበራትና የማህበራቱ መሪዎች ጋር በነበረን ግንኙነት፣ በየድርጅቶቻችን በነበረን ኃላፊነት፣ ተከሣሾች ተሳታፊ በነበርንባቸው የወጣቶች ጉዳይ ስብሰባዎችና እንቅስቃሴዎች በመሉ አንዳች እንኳን ሕገወጥ እንቅስቃሴ፣ ለአመጽ ማነሳሳት፣ ድጋፍ መስጠት ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሕገወጥ ተግባር ፈጽመን እንደማናውቅ እና ይልቁንም ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ፣ ሰላማዊና ጠቃሚ አስተዋጽኦ ስናበረክት እንደነበር በማስረዳት፣

ሠ. አዳነ በቀለ እና ወንድወሰን ስዮም የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ተከሣሾች በነገሩን መሠረት በአካባቢያችንና በየመንገዱ ያለውን ሰው ሳይቀር ለአመጽ ቀስቅሰን አደራጀን በማለት ስለተናገሩት፤ 94ኛው ተከሣሽ ዳንኤል በቀለ እነዚህን ሁለቱንም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ፍጽሞ በአይኔ አንኳን አይቼ የማላውቃቸው ሰዎች መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ 95ኛው ከተሣሽ ነፃነት ደምሴም ወንድወሰን ስዮም የተባለውን ሰው ፍጽሞ በአይኔ እንኳን አይቼ የማላውቀው አዳነ በቀለን ግን ከሃያ ዓመታት በላይ በአንድ አካባቢ አብሮ በመኖር በጉርብትና ደረጃ ብቻ የማውቀው ሰው እንጂ በተግባራችንም ሆነ በምግባራችን የማንገናኝ ሰዎች በመሆናችን ከዚህ ሰው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እነዳልነበረኝ በማረጋገጥ፣ በተለይ በእነዚህ ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ለፍርድ ቤቱ በተሰጠው ምስክርነት ፈጽሞ በሐሰት መሆኑን፣ ተከሣሾች በቀደመ ታሪካችንም ሆነ በምርጫው ዘመን በነበረን ተሳትፎዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቀው መልካም ስማችን፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ጭምር የሚታወቀው መልካም ስማችንንና ትግብርታችንን በማሳየት የዐቃቤ ሕግ ምስክርነት ፈጽሞ ሊታመን የማይችል መሆኑን በማስረዳት፣

ረ. በአጠቃላይ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃዎች የተነሱትን ጉዳዮች በሙሉ አንድ በአንድ በማስተባበል፤ የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ አጠራጣሪና ሊታመን

የማይችል መሆኑን ማስረዳት ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህም አልፈን ንፅህናችንን ሊያጠራጥር የሚችል እንኳን ሁኔታ እንደሌለ አስረድተናል፡፡

5.5. ተከሣሾች ለዚህ ፍርድ ቤት ባቀረብነው ክርክራችንና ማስረጃዎቻችን፣ በሲቪል ማህበረሰብ አባልነታችን ተሳታፊ በነበረንባቸው ስራዎቻችን፣ ለዚህ ክስ ባበቁን ድርጊቶች ምክንያቶቻችን (motives) ፣በቅንነታችን አንዳች እንኳን ሐሰት አንዳች እንኳን የወንጀል ሐሳብ ቢገኝበት ፍረዱብን!
እኛ በንፅህናችን ስለምናምን ነፃነታችንን እነደምታረጋግጡልን እናምናለን፡፡